‹‹በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ ፥ ምድረ በዳውም ስብን ይጠግባል።››

መዝ ፷፬፥፲፩

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር

ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና

ጸሐፊ

ገነት ታደሰ



በቃጠሎ የወደመው ቤተ ክርስቲያን

# በግብፅ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ላይ በተፈጠረ የኤሌክትሪክ አደጋ የምእመናን ሕይወት ማለፉ ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ

በግብፅ እምባባ ግዛ አቢ ሲፊና ኮፐቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ነሐሴ፳ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በተፈጠረ የኤሌክትሪክ አደጋ የበርካታ የምእመናን ሕይወት ማለፉን የግብፅ ጤና ሚኒስትርን ዋቢ አድርጎ ኦርቶዶክስ ኮግኔት ድረ ገጽ ዘገበ፡፡

እንደ ኦርቶዶክስ ኅግኔት ዘገባ በተፈጠረው አደጋ 41 ምእመናን የሞቱ ሲሆን ፶፫ ያህሉ ደግሞ ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ከሞቱት መካከል አብዛኛዎቹ ሕፃናት ሲሆኑ ጉዳት የደረሰባቸው ምእመናን ደግሞ ለሕክምና ወደ እምባባና አጎውዛ ሆስፒታሎች ተወስደዋል፡፡

የግብፅ ኮፐቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዎድሮስ ዳግማዊ በተፈጠረው አደጋ የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን ለተጎዱ ምእመናን መግለጣቸውን ያስታወቀው ዘገባው ጉዳዩን ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በጋራ በመሆን እየተከታተሉት መሆኑን አስረድቷል፡፡

ቅዱስነታቸው በኀዘን መግለጫቸው  ግዛ አቢ ሲፊና እምባባ አየር መንገድ አካባቢ በሰሜን ግዛ በሚገኘው ሰማዕቱ በቅዱስ መርቆርዮስ ቤተ ክርስቲያን ላይ በደረሰው የኤሌትሪክ አደጋ ሕይወታቸውን ላጡና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ምእመንና የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን ከገለጡ በኋላ በአደጋው ዙሪያ ከአካባቢው የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ከጤና ሚንስትርና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሠሩ መሆናቸውን አሳውቀዋል ሲል ዘገባው አስረድቷል፡፡

ቅዱስነታቸው ለሟች ቤተሰቦች መጽናናትን የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ደግሞ በቶሎ እንዲያገግሙ መልካም ምኞታቸውን እየገለጡና እየጸለዩ መሆኑን ያስረዳው ዘገባው የግብፅ ፕሬዘዳንት የተከበሩ አብድል ፋታህ ኤል ሲሲም ስልክ ደውለው በተፈጠረው ነገር ማዘናቸውንና ቅዱስ ፓትርያርኩን ማጽናናታቸው አመልቷል፡፡

በመጨረሻም ፕሬዘዳንቱ በስልክ መልእክታቸው የተፈጠረውን አጠቃላይ ችግርና በምእመና ላይ የደረሰውን ጉዳት በቅርበት እየተከታተሉት መሆኑን ለቅዱስ ፓትርያርኩ እንዳሳወቋቸው ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ ዜና የግብፅ ኮፐቲክ ቅዱስ ቢሾይ ቤተ ክርስቲያን በእሳት ቃጠሎ መውደሙን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ደረ ገጽ ዘግቧል፡፡ እንደዘገባው ከሆነ በግብፅ ሚኒያ ከተማ ውስጥ የሚገኘው የቅዱስ ቢሾይ ቤተ ክርስቲያን የእሳት ቃጠሎ ቢደርስበትም በምእመናን ላይ የደረሰ የአካልም ሆነ የሞት ጉዳት የለም፡፡

ቃጠሎው ወደተለያዩ አካባቢዎች ሳይስፋፋና የከፋ ጉዳት ሳያደርስ የፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር እንዳዋሉት ዘገባው ያስረዳ ሲሆን ከችግሩ በኋላ የምሥራቅ ሚኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ፋም፣የሚኒያ ከተማ አስተዳደሪ ሜጀር ጀኔራል ኡስማን አል-ቃይዳ እንዲሁም የሚመለከታቸው ሌሎች የአካባቢው የመንግሥት አካላት ለቅኝት ወደ ቦታው እንዳቀኑ ከዘገባው ለማወቅ ተችሏል፡፡





የአወርስ ካፌ ሥራ አስኪያጅ ችግር በፈጠሩበት ወቅት

# የጸሎት መጽሐፍ በቀደደው ግለሰብ ላይ ምርመራ እንዲደረግ ተጠየቀ

ካሳሁን ለምለሙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ከሆነች ወጣት እጅ የጸሎት መጽሐፍ ቀምቶ ቀዳዶ ቆሻሻ መጣያ ላይ የጨመረው በባሕር ዳር ከተማ የሚገኘው የአወርስ ካፌ (ours cafe) ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ፍቅሬ ንጉሤ ላቀው ላይ ምርመራ እንዲደረግ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ፖሊስ መምሪያን ጠየቀ።

በካፌው ውስጥ በመስተንግዶ ሥራ ላይ ተሰማርታ የምትሠራ ኦርቶዶክሳዊ ወጣት በድንገት በመታመሟ ምክንያት በቦታው የነበሩ ሰዎች ጸሎት እያደረጉላት በነበረበት ወቅት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት የካፌው ሥራ አስኪያጅ የጸሎት መጽሐፉን ቀዳደው ቆሻሻ ላይ መጨመራቸውን ሀገረ ስብከቱ አስታውቆ እንደዚህ ዓይነት ድርጊት መፈጸሙ የእምነቱ ተከታዮች በሌላው ላይ እንዲነሱ ለማድረግ የታቀደ በመሆኑ ሊታረም እንደሚገባ አሳሰስቧል።

ሀገረ ስብከቱ አያይዞም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ታሪካዊና የሀገር ባለውለታ መሆኗ እየታወቀ አንዳንድ ግለሰቦችና ድርጅቶች ልዕልናዋን ዝቅ ለማድረግ እያደረጉት ያለው ሙከራ በአስቸኳይ እንዲቆምም ሀገረ ስብከቱ ጠይቋል።

በሌላ በኩል ግለሰቡ አስነዋሪ ሃይማኖት ተኮር ችግር ከፈጸሙ በኋላ ተከራይቶ ይሠራበት የነበረውን ሕንጻ ያከራየው ዝማም ታወር አወርስ ከፌ (ours cafe) አሁንና ከዚህ በፊት በፈጸማቸው ተደጋጋሚ ጥፋቶች ምክንያት ያለበትን ቀሪ ወራኀዊ ክፍያ በመክፍል ሕንጻውን ለቆ እንዲወጣ ትእዛዝ ማስተላለፉን ገልጧል።

የተፈጠረው ችግር ድርጅታቸውን እንደማይወክልና በግለሰብ ደረጃ የተፈጸመ መሆኑን የገለጡት የአወርስ ከፌ (ours cafe) ባለቤት አቶ መንግሥቱ ጌታሁን ችግሩን የፈጠርው የካፌው ሥራ አስኪያጅ አስተዳደራዊ ርምጃ እንደተወሰደበትም ተናግረዋል።

አቶ መንግሥቱ ጌታሁን አክለውም ጉዳዩ በሕግ አግባብ እየታየ መሆኑን ጠቅሰው ካፌው ሕዝብ የሚገለገልበትና ከ፪፻ በላይ ሠራተኞች የሚተዳደሩበት በመሆኑ ካፌውን መዝጋት በድርጅቱና በሠራተኞቹ ላይ ጫና ስለሚያመጣ የሚመለከተው አካል ጉዳዩን ተመልክቶ ካፌው ወደ አገልግሎት እንዲመለስም ጠይቀዋል።

ለተፈጸመው ሃይማኖት ተኮር ጥፋት በድርጅታቸው ስም ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን ይቅርታ መጠየቃቸውን አክለው ተናግረዋል።

# በአዲስ ዘመን አዲስ ዕድል ተሰጥቶናልና በአገልግሎታችን እንበርታ

በሀገራችን አዲስ ዘመንን የምንቀበልበት የመስከረም ወር በብዙ ተፈጥሮአዊ ዑደት አዲስ የሚሆንበት፤ የደረቁ ዛፎች የሚለመልሙበት፤ ደፍርሰው የነበሩ ወንዞችና ጅረቶች ጠርተው የሚገኙበት፤ ተራቁቶ የነበረው ሜዳ፣ ሽለቆና ተራራው አረንጓዴ የሚለብስበት በተለይም በአደይ አበባ የሚደምቅበት የተለየ ወር ነው፡፡ አዲስነት በተግባር የተገለጠበት፤ ይዞት ከመጣው አሮጌነት የሚላቀቅበት፤ ከትላንት በተለየ መልኩ ራሱን ለውጦ አዲስ የሚሆንበት ወር ነው መስከረም፡፡

በሀገራችን በተለይም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በድምቀት ከሚከበሩ ታላላቅ በዓላት አንዱ አዲስ ዘመን ወይም የዘመን መለወጫ በዓል ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የምትቀበለው በተለየ መንገድ ነው፡፡ የዘመን ቀመሯን አዘጋጅታ፤ በዓመት ውስጥ የሚውሉ በዓላቷን በዓመት ውስጥ ላሉት ወራትና ቀናት አከፋፍላ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ባቀደችው መሠረት ዓመቱን ሙሉ የሚከወኑ ነገሮች ሳይዛነፉ ወደ ተግባር ይለወጣሉ፡፡ በዓላቱ አጽዋማቱ፣ ስብከቱ፣ ዝማሬው ሁሉም በተቀመጠለት የጊዜ መርሐ ግብር መሠረት ይከናወናል፡፡

ምእመናን አዲስ ዓመትን በአዲስ መንፈስ እንዲቀበሉ ነገን አቅደው የተሻለ ሥራን እንዲሠሩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዋ ትምህርት ቤት ነች፡፡ ብዙዎቻችን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ያለነው፣ የምንሠራውም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ነው፡፡ እንደ ምእመን ከፍ ሲልም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደሰጠችን መዓርግ አዲስ ዓመትን መቀበል ብቻ ሳይሆን አዲስ እቅድንም አቅደን ለመሥራት እንዘጋጃለን፡፡ ሆኖም በአዲስ ዓመት ላይ የምናቅዳቸውን እቅዶች ከፍጻሜ የምናደርሰው ስንቶቻችን እንሆን?

አቅደው ያልሠሩ፣ አዲሱን ዘመን መሻገር ያልቻሉ ብዙዎች ናቸውና ዓመት ዓመትን ተክቶ ባለፈ ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እንድንሸጋገር በማድረግ ዕድሜን ለጨመረልንና አዲስ ዕድልን ለሰጠን አምላክ ከማመስገን ባሻገር በመንፈሳዊነታችን በርትተን ዓላማ ያለው ፤ በምንም ወደ ኋላ የማይሄድ፤ ተጀምሮ የማይቋረጥ በጊዜ ቀመር የተለካ መልካም ሥራ ከእኛ ይጠበቃል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በመልእክቱ ‹‹የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና፡፡›› (፩ኛ ጴጥ.፬፥፫) እንዳለ በአዲስ ዓመት ለአዲስ አገልግሎት ስንነሣ ያለፈው ስህተታችንን ባለመድገም፣ መንፈሳዊ ዝለታችንን በጥንካሬ በመለወጥ፣ መስከረም ወር ላይ ምድሪቷን አዲስ እንደሚያደርገው የአደይ አበባ በምግባር አብበን ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የተሻለ አገልግሎት ራሳችንን አጭተን ልናዘጋጅ ይገባናል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ልጆቿ ትላንትናና ከትላንት ወዲያ በብዙ ተግዳሮት ውስጥ ማለፋቸው አዲስ የሚመጣውን ነገን ተዘጋጅተን እንድንጠብቅ ብዙ ትምህርት ሰጥቶን አልፏል፡፡ ትላንት የሳትነው ነገር ምንድነው? በቸልተኝነት ነገ እንሠራዋለን ብለን የተውነው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የቱ ነው? መድረስ ሲገባን ለሌሎች የተውነው አሊያም የሌሎች ሥራ ነው ብለን ያልሠራነውን ሥራ በውል ለይቶ

ራስን ማዘጋጀት ዛሬ የተሰጠን ዕድል ነውና ዛሬውኑ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

በተሰጠን አዲስ እድል ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል አቅደን ስንነሣ እቅዱ ከራሳችን ሕይወት እንደሚጀምር መዘንጋት ተገቢ አይደለም፡፡ የብዙ ሰዎች አገልግሎት ከፍሬው ይልቅ ገለባው የሚበዛው የራስን ሕይወት ቸል ማለትና ትኩረት ሰጥቶ ባለማገልገል ነው፡፡ ሰው ቤተ ክርስቲያንን ከትላንት በተሻለ ነገ ላይ በደንብ አገለግላለሁ ብሎ እቅድ ሲያወጣ በራሱ መንፈሳዊ ሕይወት ላይም እቅድ ሊያወጣ ይገባል፡፡ ትላንት በቁጣ፣ በክፋት፣ በሐሜት፣ በአጠቃላይ በሥጋ ሥራ ውስጥ ሆኖ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል የነበረ አገልጋይ ራሱን ለውጦ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ ያልተለወጠ ሕይወት ያላቸው አገልጋዮች በምንም መንገድ ሌሎችን ሊለውጡ አይችሉምና የእኛም ሕይወት የአዲሱ ዓመት እቅድ አካል መሆን ተገቢ ግዴታም ጭምር ነው፡፡

በቅዱስ መጽሐፍ ‹‹በዚህች ዓመት ደግሞ ተዋት›› (ሉቃ. ፲፫÷፰) በሚል ልመና አሮጌውን ዘመን አልፈን ወደ አዲሱ ዘመን እንድንሸጋገር የቅዱሳኑን ልመና የተቀበለ አምላክ ሲፈቅድልን በተሰጠን ዕድሜ በተሰማራንበት የአገልግሎት መስክ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንና የሰዎችን ልብ የሚያሳርፍ በጎ ሥራ ለመሥራት ለራሳችን ቃል መግባት ያንንም በተግባር ማሳየት ከእኛ ከክርስቲያኖች ይጠበቃል፡፡ በታማኝነት በተቀመጥንበት ቦታ ሁሉ ለሌሎች አርአያ የሚሆን ሥራን በመሥራት እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኘው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በዘመናት ዑደት ውስጥ ዘመን ሲለወጥ በስሙ የተጠራን ክርስቲያኖች ራሳችንን ለውጠንና አድሰን ከትላንትናው በተሻለ ስብእና ቤተ ክርስቲያንንና ከእኛ የሚጠብቁ ሰዎችን ማገልገል ከእኛ ይጠበቃል፡፡ አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋን የምንሰንቅበት ነውና ከምናሳምረው ቤታችንና ከምንለውጠው ልብሳችን ይበልጥ ልባችን እንዲለወጥ በመጸለይ የአመለካከት ለውጥ በማድረግ በንስሓ፣ ሥጋ ወደሙን በመቀበል አካሄዳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ እያሳለፈች ያለውን ፈተና ማንም ክርስቲያን የሚዘነጋው አይደለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከምእመናን ጋር ዛሬም በተለያየ መንገድ በስደት ላይ ትገኛለች፡፡ በመሆኑም ከእኛ ከልጆቿ የምትጠብቀው ብዙ ነገር አለና ራስን በዚያ ልክ ማዘጋጀት ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከዘመን ጋር አዲስ ሆኖ፤ ዘመኑን ዋጅቶ እና በተሰጠው አዲስ ጭማሪ ቀን ተጠቅሞ ራሱንም ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ልዕልና ሕይወት የሚያደርስ ዓላማ ይዞ አዲሱን ዘመን የሚቀበል አዲስ ክርስቲያን መሆን ይገባናል፡፡

# ቤተ ክርስቲያን ለሰላም ያላት ሚና እና በሀገራዊ የምክክር መርሐ ግብሩ ሊኖራት የሚገባት ፋይዳ ምን ሊሆን ይገባል?

ሻምበል ጥላሁን

ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለፉት አራት አሥርት ዓመታት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያሳለፍናቸው አራት ዓመታት ሰላም የራቀባቸው፣ ደም አፋሳሽ ጦርነቶች የተካሄዱባቸው ጊዜያት ናቸው። በነዚህ ጊዜያት ሰዎች ተገድለዋል፤ አካላቸው ጎሏል፤ ከቤት ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፤ ንብረቶቻቸው ወድመዋል። በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ደርሰውባታል። የሀገር ባለውለታ የሆነችው ጥንታዊቷ፣ ሉላዊቷ፣ ታሪካዊቷና ብሔራዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የሥርዓተ መንግሥት ለውጥ በመጣ ቍጥር፣ ከለውጡ ጋራ ተያይዘው በኅብረተሰቡ ላይ የሚከሠቱ ችግሮች ሰለባ እየሆነች እንደሆነም ክስተቶቹ ምስክሮች ናቸው።

ለሰላም ስትል የደረሰባትን ጉዳትና ችግር ሁሉ በትዕግሥት፣ በአርምሞና በጽሞና ማሳለፍ ከጀመረችም እነሆ ግማሽ ምዕት ዓመትን አሳልፋለች። መንግሥት ይህን ጊዜ እየጠበቀ ሀገሪቱን የሚያምሰውን የሰላም እጦት በንግግር  እፈታለሁ ሲል ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሕዝብ ተወከላዮች ምክር ቤት አቋቁሞ ወደ እንቅስቃሴ ገብቷል። በዚህ የወቅታዊ ጉዳዮች ዜና ትንታኔያችን ቤተ ክርስቲያን በምክክሩና ለሀገሪቱ ሰላም መምጣት ያላት ሚና ምንድነው? ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናን በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ሊኖራቸው የሚገባቸው ሚና ምንድን ነው? ስንል እንጠይቃለን።

አቶ ዳዊት ደስታ ‹‹ቤተ ክርስቲያን "በሰላም ግንባታ ያላት ሚና›› በሚል ርእስ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ሰላም ምንድን ነው? ብሎ ይጠይቅና ‹‹ሰላም በስምምነትና በአንድነት አብሮ መኖር ማለት ነው›› በማለት ይገልጻል። አያይዞም ‹‹የሰው ልጆች በምንኖረው ሕይወት ውስጥ እጅጉን ከሚያስፈልገን ነገር ዋነኛው ሰላም ነው።›› ይለናል። ‹‹ፍጥረታት እንዲኖሩ የሚያስፈልገው ሰላም ነው። ያለ ሰላም ልንኖር አንችልም። ሰላም ማለት ‹‹ፍጹም፣ ጤና፣ ዕረፍት፣ ዕርቅ፣ ፍቅር፣ አንድነት፣ ደኅንነት፣ ተድላ፣ ደስታ፣ ሰላምታ፣ የቡራኬ የምርቃት ቃል፣ ሰው ሲገናኝ ሲለያይ የሚለው የሚናገረው ወይም የሚጽፈው›› በማለት  አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ለሰላም የሰጡትን ፍቺ ይጠቁማል። ዳዊት። (መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ ፰፻፰፰) የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ‹‹የሰላም ግንባታ ማሠልጠኛ›› በተሰኘው ጥናታዊ መድበሉ ስለ ሰላም ምንነት ‹‹ሰላም የሚለው የአማርኛ ቃል የያዘው ፅንሰ ሐሳብ ከጦርነትና ከዐመፅ ነፃ መሆን›› ከሚለው የአንዳንድ መዛግብት ቃላት ሰፋ ያለ ትርጉም ይዟል። ‹‹ሰላም›› ለሰው ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታና ውድ ጸጋ ነው።

### ቤተ ክርስቲያን፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶች እና ምእመናን ለሀገር ሰላም ያላቸው ሚና

ፍቅረ ሥላሴ የተባሉት የኮተቤ ቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ምእመን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ለሰላም ያላቸውን ሚና አስመልክተው ‹‹የእምነት ተቋማት ባሉበት ማኅበረሰብ ውስጥ በርካታ ሚና ሊኖራቸው ይችላል›› ይላሉ። ‹‹የተቋማቱ ሚና ስፋትና ጥልቀት በአብዛኛው የሚወሰኑት የእምነታቸው ተከታዮች ብዛት፣ የአመራር፣ ከመንግሥት እና ከሌሎች የኅብረተሰቡ አካሎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እንዲሁም የተቋማቱ ዕድሜና ታሪክ ነው፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያሉ ረጅም ታሪክ፣ በርካታ ምእመናን፣ ጉልህ አገራዊና ማኅበራዊ ሚና ያላቸው የእምነት ተቋማት የኅብረተሰባቸውን ችግሮች ለማቃለል እና ሕዝቡን ለማስተማር፣ ለማስተባበር እንዲሁም የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች ለማቀራረብ ከሌሎች የተሻለ ብቃትና ተቀባይነት የሚያገኙበት ዕድል ጥቂት አይደሉም። የእምነቱ ተቋማት እና መሪዎቻቸው በኅብረተሰባቸው ውስጥ በርካታ ሚና ሊኖራቸው ይችላልም።›› ሲሉም ያስረዳሉ።

አቶ ዳዊት ደስታ በበኩሉ ‹‹ከትላንት እስከ ዛሬ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በትንሹም በትልቁም የሀገር ጉዳይ የሰላም እና የዕርቅ ማዕከል ናት። በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተደረጉ የእርስ በእርስ ጦርነቶች የተለያዩ ጎሳዎች እና ስብስቦች የታረቁት እና የሚታረቁት በሃይማኖት አባቶች ነው። በሀገራት ደረጃም ከዲፕሎማሲው ጎን ለጎን የሃይማኖት አባቶች ሰላምን በማውረድ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው። ‹‹የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና›› (ማቴ ፭፥፱) የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያን ካህናት ሁል ጊዜ በሰላም ግንባታ እና በዕርቀ ሰላም ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዘው ኖረዋል፣ ዛሬም  ወደ ፊትም ይህንን ተግባር የሚቀጥሉበት ነው›› ይላል በጽሑፉ።

በእርግጥም ሀገራችን ትላንትም ሆነ ዛሬ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ጠብ እና ጦርነቶች ሲካሄዱ ኖረዋል። ለምሳሌ ጎሳ ተኮር ጦርነቶች ከትላንት እስከ ዛሬ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ደም ሲያፋስሱ መኖራቸው በግልጽ የሚታወቅ ነው። አሁንም በየምክንያቱ እያገረሸ ሰው ከሰው እያለያየ እና ሕይወት እየቀጠፈ ነው። ለዚህ ፍቱን መድኃኒቱ ደግሞ መንግሥት ከሚወስደው የኃይል ርምጃ ይልቅ ቤተ ክርስቲያን ምእመኗን በማስተማር ሊመጣ ካለው መዓት እና ጦርነት መታደግ እንደምትችል የታመነ ነው። በዘመናችን ሁላችንም እንዳየነው በመገናኛ ብዙኃን እንደ ሰማነው በማኅበራዊ ትስስር ገጽ እንደ ተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን ያ ሁሉ መከራ ሲደርስባት መከራ አድራሾቹ ላይ ጦርነት ከመክፈት ይልቅ ለሰላም ስትጠራ ነበር። እየተቃጠለችም ሆነ ካህናቷና ምእመናኖቿ እየታረዱ እንኳን እጇን ለሰላም ዘርግታ ነበር። ይህም ቤተ ክርስቲያንም ሆነች አገልጋይ ካህናቶቿ ለሰላም ምን ያህል ዋጋ እንደሚከፍሉ ኢትዮጵያ ለሰላም እና ዕርቅ ያላትን ከፍተኛ ሚና የሚያሳይ ነው።

አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው ‹‹ቤተ ክርስቲያን እና ምእምናንን ለሰላም ግንባታ ያላቸውን ሚናዎችም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ብለን በሶስት ዋናዋና ክፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን›› የሚሉት አቶ ፍቅረ ሥላሴ የቤተ ክርስቲያንን የጎላ ሚና እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፡፡

‹‹ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታችን ጋር በጣም አስፈላጊ ነው የምለው የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ሚና ነው፡፡ በጥቅሉ ‹ማኅበራዊ› የምንለው የቤተ ክርስቲያን ሚና ከባህል፣ ከኅብረተሰብ ሰላምና የተሻለ አኗኗር፣ ችግረኞችን ከመርዳትና ከተያያዙ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ በኩል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ ታሪካዊና ትልቅ ማኅበራዊ ተቋምነቷ የማስታረቅ፣ የማቀራረብና የማስማማት ኃላፊነቷን መወጣት ይጠበቅባታል፡፡ በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያናችን በምልጃዋ ዕርቅን፣ በአስታራቂነቷ ፍቅርንና ሰላምን ማስፈኗ በከበረ ደሙ ከመሠረታት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣት የባለሟልነት መብቷ ነው፡፡›› ይላሉ፡፡

በሌላም በኩል በቤተ ክርስቲያን የሰላም ሚና የጎላ መሆኑን የሚገልጸው አቶ ዳዊት ደስታ ‹‹የሃይማኖት ተቋማት የቆሙበት መሠረት ዓለማዊ አስተሳሰብ ባለመሆኑ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ የሚኖሩ ምእመናን ሰላማዊውን መንገድ የሚናፍቁ በመሆናቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ የተበደሉ ወይም የበደሉ ወገኖች ካሉ በማስታረቅ፣ ያኮረፈ ወይንም የተገለለ ወገን ካለም የማስማማቱን ተግባር ይወጣሉ፡፡ የሃይማኖት ተቋማት የቆሙለት ዓላማም ከሀገር አልፎ በዓለም ላይ ሰላምና ፍቅር እንዲሰፍን መጸለይና መትጋት ከሁሉም በፊት ቀድሞ የሚሠራ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ሃይማኖት የሚሰበክባት ብቻ ሳትሆን ማኅበራዊ ጉዳይም የሚመለከታት ጭምር ናት›› ሲልም ያስረዳል፡፡

መንግሥት ጊዜ እየጠበቀ ሀገሪቱን የሚያምሰውን የሰላም እጦት በምክክር እፈታለሁ ሲል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁሞ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ የተቋቋመው ኮሚሽን መሪዎችም ለሀገር ሰላም መሆን ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አድርገዋል፡፡ ጥሪውን ተከትሎ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በይፋ የተሰጠ ምላሽ ባይኖርም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የገጠማትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ታሳቢ ያደረገ የኦርቶዶክሳውያን ጥያቄዎችን ለማስመለስ እየሠራሁ ነው የሚለው ‹‹ሞዐ ተዋሕዶ›› የተባለው ግብረ ኃይል ቤተ ክርስቲያን በምክክሩ ላይ ሊኖራት በሚገባት ሚና ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ይናገራል፡፡

የግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ የሆኑት መምህር ፋንታሁን ዋቄ እንደሚናገሩት ‹‹ ‹ሞዐ ተዋሕዶ› ይዞ ከተነሣው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ጥያቄዎች ባሻገር የምክክር ኮሚሽኑ ከአካባቢው ወጣቶች፣ ከአካባቢው ምሁራንና ከሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍል ጋር አብረን እንሥራ ሲል ያቀረበውን ጥሪ ተከትሎ የቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ምሁራንና ምእመናን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ያለባቸውን ማብራሪያና ጥያቄ በምን መልኩ ሊቀርቡ እንደሚገባቸው በ‹ሞዐ ተዋሕዶ› ማኅበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ጥያቄና ማብራሪያው መዘጋጀቱን›› ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም ‹‹ኦርቶዶክሳውያን ከቋንቋ፣ ከመልክዐ ምድራዊ አሠፋፈር፣ ከፖለቲካዊ ትርክት ባሻገር በአገር ውስጥ እንደሚገኝ አካል እንደዚሁም ልዩ ጉዳይና ፍላጎት እንዳለውና ፖለቲካዊና ርእዮታዊ ዒላማ ተደርጎ እንደሚጠቃ አንድ ታላቅ ማኅበረ-ሰብ ታይተን ምላሽ እንዲሰጠን ሳይረፍድ መጮኽ አለብን›› ይላሉ፡፡

በዚህ ምክክር መርህ በጥንቃቄ በማጤን እንዲሁም አሁን ያለውን የኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች እልቂትና መዋቅራዊ ጥቃት በማገናዘብ ኮሚሽኑ በጥንቃቄ ሊመለከተው ይገባል የሚሉትን ጥያቄዎች አስመልክቶ ግብረ ኃይሉ በማኅበራዊ ገጽ ትስስሩ ቀጥሎ ያሉትን አንኳር ነጥቦች ማንሳቱን ይናገራሉ፡፡

በምክክር ጉባኤው አንዱ ሊሆን ይገባዋል ያሉትን "በአካባቢው ምሁራን"፡- ምሁርነት ከዩኒቨርሳል ዕውቀት (ዩኒቨርሲቲ ተምሮ)፣ የደምና የአጥንት ወገንተኝነት ሳይረታው በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊነትና እውነትን መሠረት ያደረገ፣ የዕውቀቱና የአስተዋጽኦው ግብ የሰው ልጆችን በሰላምና በአንድነት እየኖሩ አገራቸውን ለመጪው ትውልድ በክብርና በልዕልና እንዲያስረክቡ ማስቻል ይሆናል፡፡ እኛ አገር ምሁራን ዩኒቨርሳል ዕውቀት ሳይሆን የንዑስ ማንነት ፖለቲካ ሎሌዎች ሲሆኑ ቆይተዋል የሚለው ጥያቄው፡፡ የኦሮሞ "ምሁራን"፣ "የአማራ ምሁራን"፣ "የትግሬ ምሁራን"፣ ወዘተ ተባብለው ዩኒቨርሲቲ ተከፋፍለው የየአካባቢያቸውን ፖለቲካዊ ግብ ለማሳካት የራሳቸውን የአካባቢ ትርክት በእውቀትና በሳይንስ ስም ሲያደራጁ የኖሩ ሆነዋል፡፡›› በማለትም ይሞግታል ግብረ ኃይሉ፡፡ አገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ገለልተኛ፣ በእውነትና በፍትሕ የሚመሩ፣ እውቀትን መሠረት ያደረጉ፣ ለትርክትና ለፖለቲካ የማይንበረከኩ እውነተኛ ምሁራንን እንዴት ይለያል? ሲልም ይጠይቃል፡፡

ከዚህም ባሻገር ‹‹ምሁራን› የተባሉት ባለፉት ፴ ዓመታት በተለይ ባሳለፍናቸው ፬ ዓመታት የዜጎችን እልቂትና ስደት፣ በተለይም የኦርቶዶክሳውያን ዜጎችን በመጽሐፍ፣ በኪነ ጥበብ ውጤቶች፣ በመደበኛ ትምህርት አሰጣጥ፣ በፕሮፓጋንዳ፣ በፖለቲካና በቀጥታ በአካል በማፈናቀል እና በመግደል የሚካሄደውን ግልጽ ዘመቻ አንድም ጊዜ በአደባባይ ሲቃወሙ አልታዩም›› የሚለው ግብረ ኃይሉ ‹‹ ‹ምሁራኑ› ለመከራው ምክንያት የሆኑ የሐሰት ትርክቶችን በዕውቀት ለመርታት አልሞከሩም›› ሲልም ይሞግታል፡፡ ‹‹ግፍን በዝምታ መመልከት ልማዱ ያደረገ ‹ምሁር› እና ከመጣው የፖለቲካ ዝንባሌ ጋር አብሮ የሚፈስ ሕሊና ያላቸው ሰዎችን እንዴት ፍትሓዊ የሆነ ምክክር ላይ አስተዋጽኦ ያደርጋሉም?›› ይላል፡፡

በሌላም በኩል ‹‹የአካባቢው ወጣቶች ‹በብሔር ማንነት ዘውግ› እንዲሰለፉ፣ በለጋ ዕድሜያቸው በፕሮፓጋንዳ እንዲታወሩና ጎሮቤቶቻቸውን በእሳት እስከማቃጠል፣ ተደራጅተው እኛና እነርሱ በማለት ብዙ ጥፋት ያደረሱ ወጣቶች ባሉበት ዐውድ ለፍትሕና ለእውነት የሚቆሙ ወጣቶች በምን መስፈርት ተለይተው በውይይቱ ይሳተፋሉ?›› ሲልም ኮሚሽኑን ይጠይቃል፡፡

በማከልም ‹‹ገለልተኛ ሆነው ሊያወያዩ በሚችሉ አወያዮች የሚባሉትን ለመምረጥ ምን አሳማኝ መሥፈርቶች አዘጋጅታችኋል?› የሚለው ግብረ ኃይሉ፤ ገለልተኝነት ትርጉሙ ፍትሓዊነት፣ እውነት፣ በሕዝብ ባህልና እምነት መሠረት ላይ የቆሙ ዕሴቶችን ማክበር፣ ክፋትን አጥፍቶ መልካምነትን

ማልማት ላይ አተኩረው ለሕሊናና ለፈጣሪ በመቆም የጊዜ ሰዎችን ሳይፈሩ ለትውልድ ሰላምና አንድነት መቆም ነውና "ገልለተኛ አወያይ" ስትሉ መሥፈርቱን ሕዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ ዝግጁ ናችሁ?›› ሲልም ግብረ ኃይሉ ይጠይቃል፡፡

‹‹የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ አገራዊ መድረክ ተነፍገው በወራሪነት፣ በኋላቀርነት፣ በነፍጠኝነት፣ በቀድሞ ሥርዓት ናፋቂነት፣ በአሐዳዊነት፣ ከፍ ሲል ልክ ሂትለር አርአያንና አይሁድ ብሎ ለፍጅት ሰዎችን እንደዳረገው ሁሉ በአሁኑ ግዜ በኢትዮጵያ ኩሽና ሴም የሚል ትርክት በተዘራበት ሥርዓታዊና መዋቅራዊ ጥቃት የተከፈተባቸው ኦርቶዶክሳውያን ድምጽ በፖለቲካው መዋቅርና አመራር ሳይታፈን በምክክር እንዴት ይወከላል? ወይንም የተለያዩ ፍላጎቶች እንዲወከሉ የተደረጉት በንዑስ ማንነት ለዚያውም በቋንቋና አካባቢ ጠባብ መሥፍረት በመሆኑ፣ በዚህ ጠባብ ማዕቀፍ የማይዳኘው የኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ልዩ የሆነ ሁኔታው እንዴት ከግምት ይገባል?›› ሲልም ማብራሪያ ይጠይቃል፡፡

‹‹ምክክሩ የሚካሄደው የፖለቲካ ዐውዱ ቀዳሚ፣ ነባርና ኢትዮጵያዊ ዕሴት እጅግ እንዲጠላ በሚሠራበት፣ ብዙ የሐሰት መጻሕፍት የተጻፉበት፣ ትውልድ ላለፉት ፶ ዓመታት በትምህርትና በፖለቲካ ንቅናቄ ስም ስሁት ርእዮተ ዓለምና ትርክት የተጋተበትና እውነትና ሐሰትን፣ ፍትሕንና ግፍን ለመለየት እንኳ የተቸገረበት ዐውድ ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ ዐውድ ውስጥ የኦርቶዶክሳውያንን መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊና ታሪካዊ ዕሴቶችን በመደምሰስና በአዲስ ውጭ ገብ እሳቤ በመተካት እንዲደመደም የሚያደርግ አሠራር ላለመኖሩ ምን መከላከያ አላችሁ?›› የሚለውን ሐሳብ ያነሣል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹በተሳታፊ አካላት ውስጥ የተጠቀሱት ‹የአካባቢ ምሁራንና የአካባቢ ወጣቶች› የሚል ብቻ በመሆኑ የምክክር ኮሚሽኑ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የሰ/ት/ቤት ወጣቶች፣ የአገልግሎት ማኅበራት፣ ጴጥሮሳውያንና ሞዐ ተዋሕዶ አይነት እውነትንና ሃይማኖትን ለመጠበቅና ሕዝብ ለማገልገል ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ምን ሚና እንዲኖራቸው አስቧል?››ሲልም ግብረ ኃይሉ ጠይቋል፡፡

የግበረ ኃይሉ ሰብሳቢ በማከልም ‹‹የግብረ ኃይሉ መሠረታዊ ናቸው ብሎ ያቀረበውን ጥያቄና ማብራሪያ ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ በፌስ ቡክ፣ በትዊተር፣ በቴሌግራም፣ በዩ ቲዩብ፣ በደብዳቤ፣ በሰልፍ ወዘተ ጥያቄውን መጠየቅ ይገባዋል››ይላሉ፡፡ ከነዚህ የማብራሪያ ጥያቄዎች በተጨማሪ ግብረ ኃይሉ በጥናት የለያቸው ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን አጀንዳዎች የምክክር ኮሚሽኑ አጀንዳዎች እንዲሆኑ እንደሚሠራም መምህር ፋንታሁን ተናግረዋል፡፡ አጀንዳዎቹም ከዚህ የሚከተሉት መሆናቸውን ምእመናን እንዲያውቋቸውና እንዲረዷቸውም›› አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡

ከነዚህ ዐበይት ጥያቄዎች ባሻገርም የምክክር ኮሚሽኑ የኦርቶዶክሳውያን ህልውና፣ በነጻነት እምነትን ማራመድ፣ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች መኖር አስመልክቶ፦ በሕገ መንግሥት፣ በፖለቲካ ማኒፌስቶ፣ በመደበኛ ትምህርት፣ በሚዲያና መሰል መንገዶች ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮንና ኦርቶዶክሳውያንን ለጥቃት የሚያጋልጡ መልእክቶች በአስቸኳይ በሕግ እንዲታገዱ፤ ኦርቶዶክሳውያንን ለይቶ ከሥራ፣ ከመንግሥት ኃላፊነት፣ ከሀብት ማፍራት ዕድሎች የሚያገል ከቀበሌ እስከ ፌደራል የተዘረጋው ሃይማኖታዊ መንግሥትና መዋቅር በአስቸኳይ እንዲቆምና ሃይማኖታዊ ሳይሆን ሕዝባዊ መሆኑን በተግባር እንዲያረጋግጥ፤ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን በቋንቋና በተለያዩ ዘውጎች ለመከፋፈል የሚደረገው ፖለቲካዊ ጥረት በጥናትና በምርምር ስም የሚደረጉ የመከፋፈል ዘመቻዎች እና ተግባራት እንዲታገዱ አሳስቧል፡፡

በኦርቶዶክሳውያን ላይ ያነጣጠሩ የአካል፣ የሥነ ልቡና፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የፖለቲካ፣ የማፈናቀል፣ ከአገራዊ ተሳትፎ የማግለልና የፍጅት ጥቃቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ፤ እስከ አሁን የተፈጸሙ ጥቃቶች በዝርዝር ተገልጸው አጥፊዎች ለሕግ እንዲቀርቡ እና የተጎዱት እንዲካሱ፤ በመላው አገሪቱ የተፈናቀሉ ኦርቶዶክሳውያን ወደ ቀደመ ቦታቸው እንዲመለሱ፤ "አዲሲቷ ኢትዮጵያ" በሚል ሽፋን ኦርቶዶክሳዊ አሻራዎችን የማጥፋት ፖለቲካዊ ሂደት በአስቸኳይ እንዲገታ እና በግልጽ ይቅርታ ተጠይቆ እርምት እንዲወሰድ›› ሲሉም ጠይቀዋል፡፡

የሀገሪቱን ሰላም ይመልሳል ተብሎ ተስፋ ለተጣለበት የሀገር አቀፍ የምክክር መርሐ ግብር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን ትኩረት ሰጥቶ ሊመለከተው ይገባል፡፡ ከሰ/ት/ቤት ወጣቶች፣ ከአገልግሎት ማኅበራት፣ ከጴጥሮሳውያንና ሞዐ ተዋሕዶ አይነት እውነትና ሃይማኖትን ለመጠበቅና ሕዝብን ለማገልገል ኃላፊነት ካለባቸው አካላት ጋር በመመካከር በአንድ አጀንዳ በጋራ መቆምም ይስፈልጋል፡፡ ኮሚሽኑም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ቀደም ሲል በታሪክ የነበራትን ቦታና በየደረጃው የሚገኙ አገልጋዮቿ በሀገሪቱ የሚከሠቱ አለመግባባቶችን በሰላምና በማስማማት ለመፍታት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያደረጉትን ወሳኝ እንቅስቃሴ ማስተዋል ይገባዋል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሁሉም የሀገራችን ዜጎች ዘንድ ከፍተኛ የመንፈስ ልዕልናን የተቀዳጀችበት አንዱ ምክንያትም ይሄው የማስማማትና የማስታረቅ ሚናዋና ሚዛናዊነቷ በእጅጉ ከፍ ያለ ከመሆኑ በተጨማሪም የተጎዳው እንዲካስ፣ ያጠፋው እንዲቀጣ ከዚህም አልፎ ዘላቂ ስምምነት እንዲመጣ ለማድረግ ያሳየችው ቁርጠኝነቷ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ቁርጠኝቷን ለዘላቂ የሀገር ሰላም በአግባቡ መጠቀም ከኮሚሽኑም ሆነ ከመንግሥት አጠቃላይ ለሰላሙ ወሳኝ ሚና አለን ከሚሉ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል›› የሚሉት ሰብሳቢው‹‹የምክክር ኮሚሽኑ የቤተ ክርስትያንን ሚና እና በዋናነት ቤተ ክርስቲያንን አስታኮ የሚነሡ የሐሰት ትርክቶችን ማረምና ለሀገር የዋለችውን ውለታ የሚያዘክር ሚና መጫወት ይጠበቅበታል፡፡

በኮሚሽኑ የምክክር ሂድት ሁሉ ዋና ተሳታፊ መሆንም አለባት፡፡ በተለይም አገልጋዮች የዕርቀ ሰላሙን አጀንዳዎች ለሕዝብ ይፋ በማድረግ የቤተ ክርስትያን ውክልና በምን መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ማመላከት አለባቸው፡፡ ምእመናንም የዕርቀ ሰላሙን አስፈላጊነትነትና በጥቃቶቹ በዋናነት ተጎጂ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና እነርሱ ልጆቿ መሆናቸውን በመገንዘብ ጉዳዩን በትኩረት ሊከታተሉት ይገባል፡፡ በተመቸ የድምጽ ማሰሚያ መንገድም ኮሚሽኑ ቤተ ክርስቲያን ለሀገር ግንባታ የከፈለችውን ዋጋና ውለታ የሚመጥን ቦታ እንዲሰጣት ድምጽ ሊሆኑ ይገባል ሲሉም አጽንኦት ይሰጣሉ፡፡

# እንደ እንጦንስ በምንኩስና እንደ ዮሐንስ በንጽሕና

ካሳሁን ለምለሙ

**ክፍል አንድ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የማይሽራቸው ትውልድ የማይረሳቸው ለሀገር ከፍተኛ አበርክቶት ያላቸውን ሊቃውንት በማፍራት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ አላት። በመሆኑም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያን ከሚሰጡት መንፈስን የሚያድስ መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ለሀገርና ለወገን ትርጉም ያላቸው ሥራዎችን በመሥራት ይታወቃሉ። ይህ ሥራቸውም ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችን ከምታበረክተው አስተዋጽኦ መካከል አንዱ ነው።



ወላዴ አዕላፍ ቆሞስ የኔታ ነብየ ልዑል

የዛሬው ትውልድ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን እያስተማሩ ላሉት የአብነት ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ የሆነ ዕውቅናና ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል። በተጨማሪም ትውልዱ ለአብነት ትምህርት ቤቶች ከሚሰጠው ዕውቅና ውጭ በቻለው ሁሉ ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን በመደገፍ ክፍተታቸውን መሸፈን ይገባዋል። አንዳንድ ጊዜም በተለያዩ (በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ) ሁኔታዎች ቁጥራቸው እየተመናመነ የመጣውን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ለመተካት ከፍ ሲልም ወንበር ዘርግቶ ቤተ ክርስቲያንን ሊያገለግሉ የሚችሉ ሊቃውንትን ለማፍራት አብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብቶ መማር ያስፈልጋል። ከዚህ ቀደምም ሆነ በዚህ ወቅት ሳይመቻቸው ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ያሉ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ባልተመቸ ሁኔታ በአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው የተማሩ ናቸው። ቤተ ክርስቲያንን ባልተመቸ ሁኔታ ውስጥ የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ከማመስገን ውጭ ተምሮ በአገልግሎት መሳተፍ ያስፈልጋል። ከልጅነት እስከ ዕውቀት ራሳቸውን ለአገልግሎት ሰጥተው በቅርቡ በድካመ ሥጋ የተለዩንን አባት የዛሬ የቤተ አብርሃም እንግዳ አድረገናቸዋል። እኒህ የከበሩ አባት ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል የሚባሉ ሲሆን በሕይወት ዘመናቸው ቤተ ክርስቲያንን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሲያገለግሉ የኖሩ ናቸው። አባታችን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው የተመሰከረላቸው፣ ለብዙዎቹ የዕውቀት ብርሃንን ያበሩ፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን ሁሉ በጸሎታቸው የፈወሱ፣ ለሰው ልጅ ሁሉ ዋርካ መጠጊያ ሆነው ያገለገሉ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት እንደነበሩ የሚነገርላቸው ናቸው። ለሁሉም አባት የሆኑና ለተቸገሩ የሚራሩ፣ ለራበው የሚያበሉ፣ ለጠማው የሚያጠጡ እንዲሁም ለታረዘው የሚያለብሱ የደግነት ምሳሌ የሆኑ አባት ነበሩ።

ብዙ ሠርተው ጥቂት የተነገረላቸው የደግነትና የአገልጋይነት ምሳሌ የሆኑት አባት የትወለድ፣ የትምህርትና አገልግሎት ዘመናቸውን እንዲህ በአጭሩ ልናስቃኛችሁ ወደናል። መልካም ንባብ።

## ሀ. ልደት

ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል (የኤርትራ አንድ ግዛት አስተዳዳሪና የቅዱስ ላሊበላ ቤተ ዘመድ) ከነበሩት ከአባታቸው ከባላንባራስ ታደገ አበጀ እና ከእናታቸው (የአጼ ዮሐንስ ቤተ ዘመድ) ከነበሩት ከወይዘሮ ደስታ መሸሻ በድሮ አጠራሩ በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ በቡግና ወረዳ ልዩ ስሙ ብልበላ ቂርቆስ በሚባል ቦታ በ፲፱፻፳፬

ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል ገና በለጋ ዕድሜያቸው ወላጆቻቸውን በሞት በማጣታቸው ምክንያት አጎታቸው የነበሩት አቶ ገናን አበጀ አስካለማርያም የሚባሉ ሞግዚት ቀጥረውላቸው መንፈሳዊ ትምህርት እየተማሩ በአጎታቸው ቤት በምቾትና በተድላ ኖረዋል፡፡

## ለ. የመንፈሳዊ ትምሕርት ሕይወት

ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደረስ ከአጎታቸው ከአቶ ገናን አበጀ ቤት አቅራቢያ መንፈሳዊ ትምህርት በማስተማር ላይ ከነበሩት ስመጥር መምህር ሕላዌ የንባብና ዜማ ትምህርታቸውን ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡ ከዚያም ሰቆጣ ወደምትገኘው ዘቡ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የቅኔ ትምህርታቸውን ተምረው በተጨማሪም ወደ ኮረም በማቅናት ከብፁዕ አቡነ ይስሐቅ እጅ ዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል፡፡ ከዚያም ወደትውልድ አካባቢያቸው ብልበላ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው በሊቀ ዲያቆንነት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል፡፡ ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል ለመንፈሳዊ ትምህርት ባላቸው ፍቅርና በተማሩት ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ባላቸው ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ ወደ ደብረ ዐባይ በመሄድም ቅዳሴ አስመስክረው በአክሱም ጽዮን ማርያምና በግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ገዳማት በመምህርነትና በብሕትውና ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ መኖር ምኞታቸው ስለነበረ ይህንን ምኞታቸውን ለማሳካት ከባልንጀራቸው ጋር በመመካከር በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በሊቀ ዲያቆንነት ከሚያገለግሉበት ብልበላ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተነስተው በላስታና በጋይንት አድረገው ደራ ወረዳ አፈርዋናት ሽሜ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በሚገኝ ጉባኤ ቤት በእንግድነት ባደሩበት ጊዜ በጉባኤ ቤቱ ያሳደሯቸው አባት ታላቅ የምሥጢር አባት ስለነበሩ የኔታን የት እንደሚጓዙ ከጠየቋቸው በኋላ እርሳቸውም ቅኔ ለመማር ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር እንደሚሄዱ ይነግሯቸዋል፡፡ እኒህ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው የሆኑ አባት አንተ የምትሄደው ጎጃም ሳይሆን ስማዳ ነው  በማለት ከነገሯቸው በኋላ ስማዳ ወረዳ የሚገኝ ሰኔ ግባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሚባል ደብር ከሚያስተምሩ ታላቁ የቅኔ መምህር የኔታ በትሩ አየለ ዘንድ እንዲማሩ ላኳቸው፡፡ ከእኒህ ታላቅ የበረከት አባት የተሰጣቸውን ምክር ተቀብለው ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር መሄዱን ትተው ወደ ስማዳ ወረዳ በመመለስ ከመምህር በትሩ አየለ  የቅኔ ጉባኤ ቤት የቅኔ ትምህርታቸውን ተምረው አጠናቀዋል፡፡ ከዚያም ወደ ዋድላ ወረዳ ወቂታ ማርያም በመሄድ ከመምህር ዲበኩሉ ዘንድ ቅኔ ተምረዋል፡፡ በኋላም ወደ ስማዳ ወረዳ በመመለስ ጋና ጎዳና ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ አባት ከየኔታ ጥበቡ ታየ የቅኔና የሐዲሳት ትርጓሜ ትምህርት ለአራት ዓመታት ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡

በተጨማሪ ስማዳ ወረዳ ጎሽ ሜዳ ቀበሌ አብጅር ማርያም ከአባ ገብረአብ እጅ ደግሞ ምንኩስናን ተቀብለዋል፡፡ እንዲሁም ወደ አዲስ አበባ በ፲፱፻፹ ዓ.ም በመምጣት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ዘንድ ማዕርግ ቅስና ተቀብለዋል፡፡ እንዲሁም በ፲፱፻፹ ዓ.ም በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ከብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ  ዘንድ የቁምስናን ማዕረግ ተቀብለዋል፡፡

## ሐ. የአገልግሎት ሕይወት

ጋና ጎዳና ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ከታላቁ አባት ከየኔታ ጥበቡ ታየ የቅኔና የሐዲሳት ትርጓሜ ትምህርትታቸውን እየተማሩ በነበረበት ወቅት በረዳት መምህርነት ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉ ነበር፡፡ የሰኔ ግባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መምህር የነበሩት የኔታ በትሩ በሥጋ በማረፋቸው ምክንያት በፈቃደ እግዚአብሔር የእርሳቸውን ቦታ ተክተው ዳዋ ጥሰው ቦታውን አስተካክለው፣ጎጆ ቀልሰው፣ወንበር ዘርግተው በጉባኤ  ቤቱ ለረጅም ጊዜ በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ዕንቍ የሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን አስተምረው አውጥተዋል፡፡ በርሳቸው ጉባኤ ቤት ዲያቆናት፣ ካህናት፣መናንያን፣ ተተኪ መምህራን፣ መነኮሳትና ጳጳሳት ተምረዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን በጉባኤ መምህርነት እያገለገሉ ባሉበት ወቅት በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ተደማጭ አባት ነበሩ፡፡ እረሳቸው ወደ ቦታው መጥተው ወንበር ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ የአካባቢው ማኅበረሰብ ልጆቻችንን ያስተምሩልናል፣ ይመክሩልናል፣በጸሎት ያስቡናል፣ ብለው በማሰብ ከሕጻናት እስከ አዛውንት ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከፍተኛ የሆነ አባታዊ አቀባበል አድርገውላቸው ነበር፡፡

ወንበር ዘርግተው በሚያስተምሩበት ወቅትም የቀለብ ችግር እንዳይገጥማቸው የአካባቢው ማኅረሰብ ካለው የእርሻ መሬት ቀነሶ ይሰጣቸው ነበር፡፡ ጉባኤው ሰፍቶ ተማሪዎች እየበዙና ዝናቸው ያደገ ሲመጣ እርሳቸውን ለማየት ታላላቅ አባቶች ከተለያዩ አካባቢዎች ይመጡ ነበር፡፡ አባታችን በደግነት የሚታወቁ ስለነበር የሚመጣውን እንግዳ፣የተራበና የተቸገረ ሁሉ የሚያበሉ የሚያጠጡና የሚረዱ ነበሩ፡፡ ለተማሪዎቻቸውም ልብስና ቀለብ እየሰፈሩ ያስተምሩ የነበሩ ደግ እውነተኛ አባት ነበሩ፡፡ ተማሪዎቻቸውን የቤተ ክርስቲያን ፀጋ የሆነውን የአብነት ትምህርት እያስተማሩ ጎን ለጎን የእርሻ ሥራ በመሥራት ለተማሪዎቻቸውና ለአካባቢው ማኅበረሰብ ጭምር ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እገዛ ያደርጉ ነበር፡፡

ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል ከእርሻ ሥራቸው ጎን ለጎን ወንበር ዘርግተው የአብነት ትምህርት እያስተማሩ ጫካ ለብሰው፣ጤዛ ልሰው፣ደንጋይ ተንተርሰው ፍጹም በሆነ ብሕትውና ሕይወታቸው ውስጥ ሆነው በርካታ የአብነት ተማሪዎችን ለቁም ነገር ያበቁ አባት ነበሩ፡፡ የብዙ ጸጋ ባለቤት የሆኑ እኒህ አባት እንደሐዋርያት ብዙዎችን አስተምረው ለንስሓ ሕይወት ያበቁ አባት ነበሩ፡፡ እንደ ጻድቃን የታመመን በጸሎታቸው የፈወሱ፤ እንደ አብርሃም ቤታቸውን ለእንግዳ ክፍት ያደረጉ፤እንደ ቅዱሳን በምልጃቸው አይነስውራንን የፈወሱ፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የነበሩ ሰዎችን አምላካቸው በሰጣቸው ጸጋ የፈወሱም ነበሩ፡፡ የተጨነቀ፣ የተቸገረንና ግራ የገባውን ሁሉ ያጽናኑና ይረዱ ነበር፡፡ በርካታ አድባራትና ገዳማትን ይጎበኙና ያሠሩ ነበር፡፡ አባታችን ጸሎት አድርገውለት፣ በእጃቸው ዳብሰውት፣ በመስቀላቸው አሸተውት፣ ጠበል አጥምቀው እንዲሁም ጸሎተ ማርያም አድረሰውለት ከያዘው ደዌ ካለበት ችግር ያልተላቀቀ የለም፡፡

ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል በጣም አዛኝ ከመሆናቸው የተነሳ ለሰው ለጅ ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትና ለዕፅዋት ጭምር ከፍተኛ ፍቅር ያላቸው ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት በድርቅ ምክንያት በርካታ እንስሳት ሲሞቱ የተመለከቱት እኚህ አባት ልባቸው እጅጉን በኀዘን ተሞልቶ ጸሎትና ምሕላ በማድረግ እግዚአብሔር የምሕረት ፊቱን ለእንስሳቱ እንዲያዞር አድርገዋል፡፡ በሕይታቸው ብዙ ፈተና ሲበዛባቸውም በጾም በጸሎት ፈተናውን የመለሱና አጋንትን ያንቀጠቀጡ ታላቅ አባት ነበሩ፡፡

በጸሎታቸው በረከት ያገኘ፣ፍቅራቸውንና ደግነታቸውን ያየ እንዲሁም እውነተኛ የቀለም አባት መሆናቸውን የተረዳ ሰው ሁሉ ሲያመሰግናቸውና ልዩ ክብር ሲሰጣቸው ቆይቷል፡፡ ወላዴ አእላፍ ቆሞስ የኔታ ነቢየ ልዑል በሕይወት ዘመናቸው በርካታ አኩሪ መንፈሳዊ ተግባራትን ያከናወኑ ሲሆን ወንበር ዘርግተው ያስተምሩበት የነበረው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ያረጀና የሳር ክዳን በመሆኑ በአዲስ አበባና በሌሎች የሀገራችን ክፍሎች በመዘዋወርና በጎ አድራጊዎችን በማፈላለግ ሰፊና ዘመኑን የዋጀ ሕንጻ ቤተ መቅደስ በመሥራት ለአገልግሎት አብቅተዋል፡፡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ተደርቦ ይኖር ለነበረውን የመድኃኔለም ታቦት ራሱን የቻለ ቤተ መቅድስ አሳንጸውም እንዲወደስና እንዲቀደስ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢውን ልጆች አስተምረው በማብቃት መርቀው ደብሩን እንዲያገለግሉ አድርገዋል፡፡ ለደብሩ የሚያስፈልጉ ንዋያተ ቅድሳትን በራሳቸው ወጭ አሟልተዋል፡፡

ምእመናንና አገልጋዮችን እየሰበሰቡ ሃይማኖታቸውን እንዲጠብቁና ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ በምክረ ሐሳብ ከፍተኛ እገዛ አድገዋል፡፡ በራሳቸው ወጭ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ጥንታዊነቱና ታሪካዊነቱ እንዲታወቅ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ያሉ አድባራትንና ገዳማትን ጨምሮ ቅድስት ሀገር እየሩሳሌምን በተደጋጋሚ ጎብኝተዋል፡፡ ዕድሜ ዘመናቸውን ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ባደረባቸው ሕመም በተወለዱ በ፺ ዓመታቸው ከዘህ ዓለም ድካም ዐርፈዋል፡፡ ወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ተማሪዎቻቸው በተገኙበት በሰኔ ግባ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡ የአባታችን በረከት ይደርብን አሜን፡፡

# ማእከላት ለቤተ ክርስቲያን አሳቢ የሆኑ ተቆርቋሪ ወጣቶችን አፍርተዋል

ካሣሁን ለምለሙ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በቅዱስ ሲኖዶስ ዕውቅና አግኝቶ በይፋ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ፴ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ሲያገለግል ቆይቷል። አሁንም እያገለገለ ይገኛል። አገልግሎቱ በሀገር ውስጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የክርስቶስ ወንጌል በመላው ዓለም እንዲዳረስ ይተጋል። ለአገልግሎቱ መጠናከርና መስፋፋት ከሚያግዙት አደረጃጀቶች ማካከል ደግሞ በሥሩ ያሉ ማእከላት፣ወረዳ ማእከላት፣ግንኙነት ጣቢያዎችና ንዑሳን ማእከላት ናቸው። እነዚህና መሰል አደረጃጀቶችን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያን የሰጠችውን ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ አደራ በአግባቡ እየተወጣ ይገኛል። የማኅበሩ ጥረት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚታይና የሚዳሰስ ለውጥ አምጥቶ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በመላው ዓለም በአግባቡ እንዲዳረስ፣የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ክብርና መብት እንዲጠበቅ አስችሏል።

ማኅበረ ቅዱሳን በርካታ ፈተናዎችን እየተሻገረ በቤተ ክርስቲን የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣቱ ለአገልግሎት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። በተለይ ወጣቱ ትውልድ ራሱንና ቤተሰቡን ወደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲመልስና ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር እንዲያዞሩ ያደረገበት መንገድ አገልግሎቱን ዘመን ተሻጋሪ ያደረገዋል። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ወጣቶች አልባሌ ቦታ ከመዋልና በባዕድ አምልኮ እንዳይወሰዱ በኦርቶዶሰዊ አስተምህሮ እንዲያድጉ እያደረገ ሲገኝ በግቢ ጉባያኤትና በማእከላት አገልግሎት ላይ እየተሳተፉ ያሉ ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን ተስፋዎች ብቻ ሳይሆኑ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ራሳቸውን የተሰጡ ናቸው።

በዛሬ የቃለ መጠይቅ ዐምዳችን የማእከላትን የአገልግሎት እንቅስቃሴና ተግዳሮቶቻቸውን የምንቃኝ ይሆናል። ለቅኝታችን ያመቸን ዘንድ ደግሞ በማኅበረ ቅዱሳን ለዐስራ አምስት ዓመታታ ያገለገሉትንና በአሁኑ ወቅት የማእከላት አቅም ግንባታና አባላት አገልግሎት ማስተባበሪያ ምክትል ኃላፊ የሆኑትን



ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን

ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን ጋብዘናቸዋል። ከእረሳቸው ጋር ያደረግነውን አጭር ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

**ስምዐ ጽድቅ፡-** በማኅበረ ቅዱሳን የአገልግሎት ታሪክ ውስጥ ማእከላት በምን ሁኔታ ላይ ተመሥርተው ይደራጁ እንደነበር ቢገልጹልን?

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ማእከላትን የሚመሠርትበት የራሱ የሆነ መመሪያ አለው። ማእከላት ከሚመሠረቱበት ዋና ዋና መነሻ ጉዳዮች መካካል የመጀመሪያው የአህጉረ ስብከት መመሥረት ነው። ማእከላት አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት

የአህጉረ ስብከትን መዋቅር ተከትለው በመሆኑ ለማእከላት መቋቋም አህጉረ ስብከት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ በሀገረ ስብከት ያልተደራጁ አካባቢዎች ማእከላት የላቸውም፤ ምንአለባትም ከማእከላት በታች የሆኑ (የግንኙነት ጣቢያዎችና የወረዳ ማእከላት) አደረጃጀቶች ወይም መዋቅሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ መሠረት ማእከላት አህጉረ ስብከት የሚያካልሉትን የአገልግሎት መዳረሻ እየተከተሉ አገልግሎት ሲፈጽሙ ቆይተዋል፤ እየፈጸሙም ይገኛሉ፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ አካሄድ ማእከላትን ሲመሠርትና ሲመራ ቆይቷል፡፡ ሁለተኛው መነሻ ምክንያት ደግሞ የአባላት ቁጥር ሁኔታ ሲሆን በአካባቢው ያለው የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ሁኔታና የምእመና ቁጥር ብዛት ታይቶ ማእከላት ሊደራጁ ይችላሉ፡፡ ከተደራጁ በኋላም ማኅበረ ቅዱሳን በሚያስቀምጠው የማእከላት የአገልግሎት የትኩረት አቅጣጫ ይመራሉ፡፡

ማእከላት የሚደራጁበት ዋና ዓለማ ማኅበረ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ተፈጻሚ ለማድረግ የግድ የአገልግሎት መዋቅር ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በማእከላት፣ በወረዳ ማእከላትና በግንኙነት ጣቢያዎች በኩል የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ተፈጻሚ በማድረግ የተቋቋመለትን ዓላማ ከግብ ያደርሳል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ታሳቢ አድርጎ በማእከላት በኩል አገልግሎቱን ይፈጽማል፡፡ ዋናው ጉዳይ ደግሞ ማኅበሩ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ በመላው ዓለም ተደራሽ ወይም ተግባራዊ ለማድረግ በዋናነት የማእከላትን መዋቅራዊ አደረጃጃት ይጠቀማል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- አጠቃላይ ምን ያህል ማእከላት አሉ? የማእከላት የእርስ በርስ ግንኙነትስ ምን ይመስላል?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** አሁን ባለው ሁኔታ በሀገር ውስጥ አጠቃላይ ሃምሳ ማእከላት የሚገኙ ሲሆን በውጭ ሀገራት ድግሞ ስድስት ማእከላት ይገኛሉ፡፡ በውጭ ሀገራት ካሉ ማእከላት ተጠሪነታቸውን ለዋናው ማእከል ያደረጉ ፴፫ ግንኙነት ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ አውሮፓ፣አሜሪካ፣ኬኒያ፣ደቡብ አፍሪካ ካናዳ፣ሩቅ ምሥራቅና የመሳሰሉት በውጭ ሀገራት የሚገኙ ማእከላት ናቸው፡፡ ሰሜን ሱዳን፣አቡዳቢና አውስትራሊያ ደግሞ ግንኙነት ጣቢያዎች ናቸው። ሀገር ውስጥ ያሉት ሃምሳ ማእከላት በሥራቸው ፬፻ ያህል ወረዳ ማእከላት አሏቸው፡፡ ከመቶ ሰማንያ በላይ ግንኑነት ጣቢያዎች ደግሞ ይገኛሉ፡፡ በውጭ ሀገራትም እንዲሁ በርካታ ግንኙነት ጣቢያዎችና ንዑሳን ማእከላት አሉ፡፡

የማእከላት ተናባቢነትና የእርስ በርስ ግንኑነትን በተመለከተ ማእከላት ወረዳ ማእከላትን፣ግንኙነት ጣቢያዎችንና ንዑስ ማእከላትን ይመራሉ ያስተባብራሉ፡፡ በመካከላቸው ባለው መዋቅር አማካይነት የእርስ በርስ ግንኙኘታቸውን አጠናክረው አገልግሎታቸውን ይፈጽማሉ፡፡ ማእከላት ግቢ ጉባኤያትን፣ ወረዳ ማእከላትን፣ግንኙነት ጣቢያዎችንና ንዑስ ማእከላትን የመደገፍ፣በተለያዩ ሥልጠናዎች የማብቃት፣የመገምገም፣የመምራት፣ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲወጡ የማትጋት እና የመሳሰሉት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን ስልታዊ ዕቅድ ተናባቢ በመሆኑ ከማእከላት ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ላሉ የመዋቅር አደረጃጀቶች ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የመዋቅር ተናባቢነት የሚመነጨው ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ሲሆን ያሉት አደረጃጀቶች በሙሉ በመዋቅሩ አማካይነት እርስ በርሳቸው ተደጋግፈውና ተናበው አገልግሎታቸውን ይፈጽማሉ፡፡

ማእከላት ተናበው እንዲሠሩ ከሚያግዛቸው መካከል የማኅበረ ቅዱሳን ስልታዊ ዕቅድ እስከ ታች ድረስ በሁሉም መዋቅር ላይ ተግባራዊ መሆኑ ነው፡፡ አገልግሎቱ በራሱ ተብብርና እገዛ የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም የማእከላት አገልግሎት ተፈጻሚ የሚሆኑት በሁሉም

አካላት ትብብር ነው። በአጠቃላይ ተግባራቸውና ኃላፊነታቸው ማእከላትን በእርስ በርስ ትስስር የተጠናከሩ አድርጓቸዋል። በተጨማሪም አንዱ ማእከል ከሌላው ጋር ሚያደርገው ትስስርና የልምድ ለውውጥ በመኖሩ አገልግሎቱ የበለጠ ተደራሽና በትክክል ተፈጻሚ እንዲሆን አግዟል። መምህራንን፣ አሠልጣኞችን፣ ቁሳቁስና ሌሎች ግብዓቶችን የመዋዋስ ሁኔታ መጠናከሩ ደግሞ የእርስ በርስ ግንኙነቱ የበለጠ እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- የማእከላት ስልታዊ ዕቅድ አፈጻጸም እንዴት ይለካል? በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎታቸው የተዳከመ ማእከላትስ በአገልግሎታቸው እንዲጠነክሩ እየተሠራ ያለው ሥራ ምንድ ነው?**

**ዲያቆን አስቻለሁ ጥላሁን፡-** ማኅበረ ቅዱሳን ራሱን የቻለ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ማድረጊያ ዘዴ አለው። ከታች ማለትም ከግንኙነት ጣቢያዎች ጀምሮ እስከ ወረዳ ማእከላት ያለው የአገልግሎት አፈጻጸም ለዋናው ማእከል በየጊዜው ሪፖርት ይደረጋል፤በዚህ ሁኔታ በተለይ የማእከላትን የአገልግሎት አፈጻጸም የሚገመግመው ወይም የሚለካው በየማእከላቱ ያለው ሥራ አስፈጻሚና ጠቅላላ ጉባኤ የሚባሉ አደረጃጀቶች ናቸው። ማእከላት ወረዳ ማእከላትንና ግንኙነት ጣቢያዎችን የአገልግሎት አፈጻጸም ከገመገሙ በኋላ ለዋናው ማእከል ያስገባሉ። በመጨረሻ የዕቅድ አፈጻጸሙ በዋናው ማእከል ዕቅድና ፕሮጀክት ክትትል ክፍል በኩል ይገመገማል። ይህ ሲባል ግን ማእከላት፣ወረዳ ማእከላትና ግንኙነት ጣቢያዎች የራሳቸውን ዕቅድ አፈጻጸም አይገመግሙም ማለት ግን አይደለም። አጠቃላይ ከግንኙነት ጣቢያዎች ጀምሮ እስከ ዋናው ማእከል ያሉ መዋቅሮች እያንዳንዱን ማእከላት የአገልግሎት አፈጻጸም በጥንቃቄ ይገመግማሉ፤ይለካሉ።

ማእከላት በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ በሆኑ ሁኔታዎች አገልግሎታቸው ሊዳከም ይችላል። በዚህ ወቅት አገልግሎታቸው የተዳከመ በርካታ ማእከላት በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ። የማእከላትን አገልግሎት ካዳከሙት መነሻ ምክንያቶች መካከል ዋናው በዚህ ወቅት በመላ ሀገራችን እየተስተዋለ ያለው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ናቸው። ለአብነትም በሰሜንና በምእራብ የሀገራችን ክፍሎች ያለው የሰላም እጦት ምእመናን እንዳይረጋጉ፣ቤተ ክርስቲያን የዘወትር አገልግሎቷን እንዳትፈጽም እንዲሁም ማእከላት የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት እንዳይደግፉ ሆናዋል። የሰላም እጦቱ አጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል። ማእከላትም ሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዩች በፈለጉት ሁኔታ ተንቀሳቅሰው ቤተ ክርስቲያንን ሚያገለግሉበት ሁኔታ ባለመኖሩ ለቤተ ክርስቲያንና ለማእከላት አገልግሎት መዳከም ከፍተኛ ደርሻ አለው። በየጊዜው በሚከሰተው ጦርነትና የጸጥታ ችግር ምክንያት የማእከላት አባላትና ምእመናን የተሻለ ሰላም ወዳለበት ቦታ ስለሚሰደዱ በሰው ኃይል እጥረት አገልግሎቱ የበለጠ እንዲጎዳ ያደረገዋል። ከሰላም እጦት በተጨማሪ ማእከላት በሰው ኃይል እጥረት፣ በቁሳቁስ ችግርና በበጀት እጥረት ይፈተናሉ። በዚህ የተነሳ አጠቃላይ በማእከላት ላይ ያለው ነባራዊና አሁናዊ ሁኔታ በችግር ውስጥ እንዳሉ የሚያመላክት ነው። ይሁንና የማእከላትን ችግር ለመቀነስ ማኅበረ ቅዱሳን የቻለውን ሁሉ ሲያደርግ ቆይቷል፤እያደረገም ይገኛል። ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎታቸው በጸጥታ ችግር ምክንያት የተዳከሙ ማእከላትን በመቃኘት ሁለንተናዊ ድጋፍ አድረጎላቸው የተሻለ አገልግሎት እንዲፈጽሙ ሲያደርግ ቆይቷል። በወቅቱ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎች በመስጠት፣ የአባላት ማነቃቂያ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ፣ የሰው ኃይል በማሟላት መእከላት እንዲጠነክሩና የተሻለ የአገልግሎት አፈጻጸም እንዲኖራቸው ሲያደርግ ቆይቷል። አሁንም ቢሆን ማኅበሩ ሚያደርገው የማእከላት ድጋፍና ክትትል እንደቀጠለ ነው።

# ዘመን መለወጫ (ዕንቍጣጣሽ)

እህተ ሚካኤል

ልጆች! እንዴት ከረማችሁ! እግዚአብሔር ይመስገን! እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ! ልጆች! ዛሬ የምንነግራችሁ ስለ ዘመን መለወጫ (ዕንቍጣጣሽ) ታሪክ ነው በጥሞና ተከታተሉን!



ዕንቍጣጣሽ

ልጆች! የዘመን መለወጫ በግእዝ ‹‹ዓውደ ዓመት›› ይባላል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ዕንቍጣጣሽ እየተባለም ይጠራል፡፡ የዘመን መለወጫ (ዕንቍጣጣሽ) በሀገራችን በኢትዮጵያ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ የዘመን መለወጫ የምንለው አሮጌው ዓመት አልቆ አዲሱ ዓመት የሚጀምርበት ነው፡፡ ወንዞች ከድፍርስነት የሚጠሩበት፣ ጋራው ሸንተረሩ በአረንጓዴ ቅጠል የሚሸፈንበት በተለይ ደግሞ አደይ አበባ በምድር ላይ ፈክቶ የሚታይበት ወቅት ነው፡፡

ልጆች! የዘመን መለወጫ ሁሌም በየዓመቱ የሚከበረው መስከረም ወር ላይ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚነግሩን የዘመን መለወጫ መስከረም ወር ላይ የሆነው ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜን ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው፡፡ በመጽሐፈ ሔኖክ ፳፩÷፴፱ ላይ ‹‹ለዘመን መታወቂያ ይሆን ዘንድ ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብትን ፈጠረ›› እንዳለው በዚያ ምሳሌነት የዘመን መለወጫው ወቅት መስከረም ወር ነው፡፡

ልጆች! በመስከረም ወር ቀንና ሌሊቱም እኩል ፲፪ ሰዓት ይሆናል፡፡ በሌላም በኩል ‹‹በመጀመሪያው ወር ምድር ታየች የንፍር ውኃም ከምድር ደረቀ›› ኩፋ ፯÷፩ እንዳለ በዘመነ ኖኅ ምድር በንፍር ውሃ ተጥለቅልቆ ብዙዎች ከጠፉ በኋላ ውሃው ቆሞ ምድር ደረቅ የሆነችበት ወር መስከረም በመሆኑ ሊቃውንት በዚህ ታሪካዊ ምሳሌነት ዘመን መለወጫን በመስከረም ወር ያከብራሉ፡፡

ልጆች! የዘመን መለወጫ በሌላ በኩል ‹‹ዕንቍጣጣሽ›› በመባልም ይጠራል፡፡ ዕንቍጣጣሽ የሚለው ስያሜ የመጣውም አባታችን ኖኅ ለሦስቱ ልጆቹ አህጉራትን ሲያከፋፍላቸው ለአንደኛው ልጁ ለካም የደረሰው የአፍሪካ ምድር ነበር፡፡ ካምም በዕጣ ወደደረሰው ወደ አፍሪካ ምድር ሲደርስ ወሩ መስከረም ነበርና በምድሪቱ ልምላሜ ተደንቆና ደስ ብሎት ‹‹ዕንቁ ዕጣ ወጣሽልኝ›› ብሏታልና የመስከረም ወር ዕንቁጣጣሽ የሚለውን ስያሜ እንዳገኘ ሊቃውንቱ ያስረዳሉ፡፡

ልጆች! ሌላው የ‹‹ዕንቍጣጣሽ›› ስያሜም

ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ከንግሥተ ሣባ ጋር ይገናኛል፡፡ ንግሥተ ሣባ የንጉሥ ሰሎሞንን ዜና በሰማች ጊዜ በጆሮዋ የሰማችውን በዓይኗ ለማየት ፈልጋ ብዙ ወርቅና ብር፣ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት ይዛና ሠራዊቷን አስከትላ ወደ ኢየሩሳሌም ከንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ ተጉዛ ነበር፡፡ ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር እንደተገናኘችም የወሰደችለትን ገጸ በረከቶች ሰጠችው፡፡ እርሱም ቤተ መንግሥቱንና በቤተ መንግሥቱ የሚገኙ እጅግ በጣም የከበሩ ዕቃዎችን ካሳያት በኋላ ‹‹ዕንቍ ለጣትሽ›› ብሎ እጅግ የከበረ ዕንቍን ሰጣት ወሩም የመስከረም ወር ነበረ፡፡ በዚያም የመስከረም ወር ዕንቍጣጣሽ ተብሏል፡፡

ልጆች! የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በየዓመቱ የሚመጣውን የመስከረም አንድ በዓል በዐራቱ ወንጌላውያን ስም ማለትም አንዱን ዓመት በአንዱ ወንጌላዊ በመሰየም ዘመነ ማቴዎስ፣ ዘመነ ማርቆስ፣ ዘመነ ሉቃስና ዘመነ ዮሐንስ እያሉ ያከብሩታል፡፡ የዚህም ታሪካዊ መነሻው ጌታችን መድኃኒታችን ኢሉስ ክርስቶስ በዘመነ ዮሐንስ ተፀንሶ፣ በዘመነ ማቴዎስ ተወልዶ፣ በዘመነ ማርቆስ ተጠምቆ፣ በዘመነ ሉቃስ ተሰቅሎ የሰውን ልጅ በሙሉ ከኃጢአት ቀንበር አላቋል በማለት ታሪኩን ከዐራቱ ወንጌላውያን ጋር ያዛምዱታል፡፡

ልጆች! የዘመን መለወጫ በዓል ‹‹ ቅዱስ ዮሐንስ›› እየተባለም ይጠራል፡፡ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማጥመቅ ወደ ዮርዳኖስ ባሕር ሲመጣ በምድረ በዳ የንስሓን ስብከት እየሰበከ፣ ሰዎችን እያስተማረ ነበር፡፡ ‹‹ ከዘመነ ፍዳ ወደ ዘመነ ምሕረት የምትሸጋገሩበት ጊዜ ነውና በወንጌል አምናችሁ ንስሓ ግቡ›› እያለ ያስተማረበትን ለማሰብ ‹‹ቅዱስ ዮሐንስ›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን ዘመን ወይም አሮጌው ዘመን ማብቃቱን እንዲሁም የሐዲስ ኪዳን አዲስ ዘመን መምጣቱን በመጀመሪያው አዋጅ እየነገረ የመጣ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የበዓላትን ድንጋጌ በወሰኑበት አንቀጽ የመጥምቁ ዮሐንስ መታሰቢያ በዓል አዲስ ዓመት በሚከበርበት እንዲከበር፣ በየዓመቱ የዘመኑ መጀመሪያ በእርሱ ስም እንዲጠራ አድርገዋል (ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ገጽ ፩-፫)፡፡

ልጆች! በዘመን መለወጫ በዓል ሕፃናት ባህላዊ ልብስ ለብሰው ቄጤማና አደይ አበባ በመያዝ በየቤቱ እየዞሩ በመስጠትና ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› በማለት በዓሉን በምስጋና እና በምርቃት ያከብሩታል፡፡ ልጆች! ስንቶቻችሁ ይህንን በዓል በየሰፈሩ እየዞራችሁ ርጥብ ቄጤማ በማደልና በመዘመር አክብራችኋል? ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድና ቅዳሴ በማስቀደስ በዓሉን በደንብ ልታከብሩ ይገባል እሺ ልጆች!

ልጆች! ሌላው በዘመን መለወጫ ወይም በዐዲስ ዓመት የሰው ልጆች ሕይወትም ሊለወጥ ይገባል፡፡ እናንተም በሚቀጥለው ዓመት ጎበዝ ተማሪዎች ሆናችሁ በትምህርታችሁ በርትታችሁ ለጥሩ ውጤት ልትበቁ ይገባል፡፡ ለወላጆቻችሁ የማትታዘዙ ልጆች በአዲሱ ዓመት ታዛዥ ወላጆችና ጎረቤቶች የሚወዱን ልጆች ልትሆኑ ይገባል፡፡ በተለይ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ መንፈሳዊ ትምህርትን መከታተል፣ እንደ አቅማችሁ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ለቤተሰባችሁና ለጉረቤቶቻችሁ የምትታዘዙ፣ የምትወደዱ ልጆች እንድትሆኑ በዐዲሱ ዓመት ራሳችሁን ለውጣችሁ ልትገኙ ይገባል እሺ ልጆች!

**በዓሉን የሰላም፣ የበረከትና የደስታ ያደርግልን ዘንድ መልካም ፈቃዱ ይሁንልን!**

# በእንተ ቅዱሳት ሥዕላት

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላትን ክብር ሰጥታ በተገቢው ቦታ ታስቀምጣቸዋለች። በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ እንዲሰጣቸው በማድረግም ለአገልግሎት ቦታ እንዲኖራቸውም ታደርጋለች። ኦርቶዶክሳውን ከሥዕላት አሣሣል ጀምሮ እስከ አጠቃቀም ድረስም የራሳቸው ሥርዓት አላቸው።

ይህ ደግሞ አሁን የመጣ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ የነበረና የቅዱሳት መጻሕፍትና የትውፊት መሠረት ያለው ሥርዓት ነው።

በመሆኑም አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ውስጥ ቅዱሳት ሥዕላትን እንደ የሥርዓቱ በመሣል ይጠቀማሉ። ከዚያ ባሻገር ምእመናን በየግል ጸሎትና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ቅዱሳት ሥዕላትን እንዲጠቀሙ ይደረጋሉ።

ቅዱሳት ሥዕላት ለማስተማር፣ ለምስጋና፣ ለጸሎት፣ ለምስክርነት አገልግሎት ይውላሉ። የእግዚአብሔርን ቃል፣ ሥራና ተኣምራቱን በማመልከት በመመስከር አገልግሎት ይሰጣሉ። የእግዚአብሔርን ቅዱሳን ክብር፣ ጥሪ፣ ተጋድሎ፣ ድል፣ ጸጋ፣ ቃል ኪዳን በመዘከርም ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስንና አዋልድ መጻሕፍትን ለማስተማር ሚና አላቸው።

ቅዱሳት ሥዕላት በተለይም በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ሥዕላት በካህናት ጸሎት ከብረው ተቀድሰው አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው በእነሱ ስለሚከብረው እግዚአብሔርና ስለቅዱሳኑ ታላቅ ጸጋ የተኙሣ ተኣማራትም ይደረግባቸዋል። በቅዱሳት ስእላቱ ፊት የተፈወሱ፣ እግዚአብሔርንነቁቅዱሳኑን ክብር የጠገለጠላቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። ከእግዚአብሔር ርድኤት በረከትን ያገኙ፣ በየቅዱሳኑን በረከት ጠሳተፉ ብዙዎች ናቸው።

በመሆኑም ቅዱሳት ሥዕላት የሚያዙበትና ጥቅም ላይ የሚውሉበት መንገድ ጥንቃቄ ይፈልጋል። ከፍተኛ ትሕትናና የእምነት ሕይወት ይፈልጋል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ ምእመናን ዘንድ በቅዱሳት ሥዕላት አያያዝ በኩል የሚታዩ ድክመቶች የሚያስተዛዝቡ ናቸው።

ቅዱሳት ሥዕላት በክብር መያዝ ያለባቸው ሲሆኑ፣ እንደ ተርታ ነገር ክብር አሳጥተው የሚይዟቸው ሰዎች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ቅዱሳት ሥዕላትን የምናስቀምጥባቸው ሥፍራዎች ላይ ጥንቃቄ አለማድረግ ከፍተኛ ችግር ነው። ሥዕላቱን ከፎቶና ከዓለማዊ ሥዕሎች ጋር እያጫፈሩ በተገኘበት ማስቀመጥ ትዝብት ላይ የሚጥል ነው። ቅዱሳት ሥዕላት ቅዱሳት /የተለዩ/ ስለተባሉ በተለየ ክብር በምንሰጥበት ቦታ ከሌሎች ዓለማዊ ነገሮቻችን ለይተን ማስቀመጥ አለብን።

ቅዱሳት ሥዕላት ያለአገልግሎት የሚቀመጡ ተርታ ጌጦች አይደሉም። ቤታችን በምንጠቀምበት ጊዜም ቢሆን ሥዕላት ቤታችንን ያስጌጣሉ ብለን ሳይሆን የምናመሰግንባቸውና የምንጸልይባቸው ናቸው ብለን ለፍጹም መንፈሳዊ አገልግሎት ለይተን ማክበር ይገባል።

ሌላው አስተዛዛቢ ነገር ቅዱሳት ሥዕላትን ለመቀደድ፣ በአቧራ ለመልበስ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ማስቀመጥ ነው። ሥዕላትን በትጋት እንጂ በስንፍና መንፈስ መያዝ ተገቢ አይሆንም። ሥዕሉ የሚወክለውን ቅዱስ ወደን፣ አክብርን የያዝነው ሥዕል እስከሆነ ድረስ ፍቅራችንን በሚገልጽ መንገድ መንከባከብ መጠበቅ ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም በጊዜ ብዛት ወይም ከአያያዝ ጥንቃቄ ማጣት በመነጨ የተጎዱ ሥዕላትን የምናስወግድበት ሥርዓትን ማወቅ ይገባል። በመቀደድ፣ አቧራ በመልበስ፣ በመሰበር፣ ቀለማቸው በመደብዘዝ ወዘተ የተጎዱ ሥዕሎችን አለግባብ በየሜዳው የሚጥሉ፣ እንደሌላ ወረቀትና ጨርቅ በየቅርጫቱ የሚከቱ ሰዎች ትዝብት ውስጥ ገብተው እናገኛቸዋለን።

አንዳንዶች ደግሞ በመጠን አነስተኛ የሆኑ ሥዕላትን ገዝተው በየጸሎት መጻሕፍቶቻቸው ከተው ይጠቀማሉ፤ ነገር ግን ከየመጻሕፍቶቻቸው እየተዝረከረኩ በመውደቅ የሚረገጡ፣ በቤታቸው በየክፍሉ ተንጠባጥበው የሚታዩ ቅዱሳት ሥዕላት ያጋጥማሉ። ይህንንም ማድረግ ክብር ማሳጣት ከመሆኑም በላይ ሰዎች ያለቸውን እምነትና የሚሰጡትን ክብር እንዲንቀንሱ ያደርጋል።

ሌላው አስተዛዛቢ ነገር ቅዱሳት ሥዕላት ለሥጋዊ ተግባሮቻችን በምንጠቀምባቸው መጠጫ ኩባያዎች፣

መብሊያ ሳህኖች ወይም ሌሎች የንግድ ሸቀጦች ላይ ታትመው በገበያ ላይ ሲታዩ ፍቅራችንን የገለጽን መስሎን ገዝቶ ለመጠቀም መሞከር ነው፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ነጋዴዎች መተባበር በሌሎችም ቁሳቁሶች ላይ ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈጽሙ ማበረታታት ይሆናል፡፡

በስቲከር መልክ ተዘጋጅተው በእጅ ሰዓቶቻችን፣ በመኪና መስተዋቶቻችን፣ በየመስኮቶቻችንን መስተዋቶች፣ በቢሮ ኮምፒዩተሮቻችን ወዘተ የሚለጠፉትም ቢሆኑ ደብዛቸው እስኪጠፋ ፀሐይ ሲመታቸው ንፋስ ሲገርፋቸው ዝም ብሎ መመልከት፣ በላብ ወርዝተው፣ ቅርጽና መልካቸው ጠፍቶ እስከሚታዩ አቃሎ መያዝም ያስተዛዝባል፡፡ ሥዕላቱን ለመጠቀም መፈለጉ ሳይሆን ክብር ሰጥቶ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በቢሮ ያሉ ኮምፒዩተሮች ላይ የሚለጠፉ ስቲከሮች ኮምፒዩተሮቹ ከአንደ ሰው ወደ ሌላው ሲዘዋወሩ በማያምኑ ሰዎች እጅ በመግባት እንዲረገጡና ተቀደው እንዲጣሉ ይደረጋል፡፡

ሌላው በቤት ውስጥ ባሉ ቅዱሳት ሥዕላት ልጆቻችን ከቅዱሳን ጋር ማስተዋወቅ የምንችልበት አጋጣሚ ሆኖ ሳለ ስለሥዕላቱ ክብር እና ሊደረግላቸው ስለሚገባ ጥንቃቄ ሳናስረዳቸው ቀርተን ሲጽፉባቸው፣ ሲቀዷቸው ማግኘት ከባድ ችግር ነው፡፡

ሌላው አሳሳቢ ችግር በቤቶቻችን የምንጠቀማቸውን ሥዕሎች ምንነት አለመገንዘብ እና መምህራንን ጠይቀን ስንረዳ፤ ሥዕላቱ በኦርቶዶክሳውያን የአሣሣል ዘይቤ የተሠሩ መሆን አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በነገረ ሃይማኖትም የተለየ መልእክት የሚያስተላልፉ፣ የመናፍቃንን አስተምህሮ የሚገልጡ ሥዕሎችን አደባልቆ የመጠቀም ድክመት አለ፡፡ የሮማ ካቶሊክና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት ሥዕላት በዚህ ረገድ ፈታኝ ሆነው በምእመናናን ዘንድ ችግር ያስከተሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ መቆየት ሥዕላቱን ለምደናቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው አድርግን ልንወስዳቸው እንችላለን፤ ለልጆቻችንንም አጉል ሐሳብ እንተክልባቸዋለን፡፡

ሌላው አሳሳቢው ነገር በነጠላ ላይ የሚታተሙ ቅዱሳት ሥዕላትን በስፋት የመጠቀም ነገር ነው፡፡ ለሕንፃ ማሠሪያ ወይም ለአገልግሎት መስጫ ገቢ ለማሰባሰብ አንዳንዴም በግለሰቦች የገቢ ምንጭነት በነጠላና ቲሸርቶች ላይ የሚታተሙ ሥዕሎች ትዝብት ላይ በሚጥል መንገድ መንችከውና ደብዝዘው ማየት የሚያስወቅስ ነው፡፡ በልብስ ላይ የሚታተሙ ሥዕሎች ልብሱ ሲቆሸሽና በአግባቡ ባላስቀመጥነው ቁጥር እያቀለልናቸው እንደሆነ ማሰብ ይገባል፡፡

በበዓላት ጊዜና የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎት መርሐ ግብሮች በተዘጋጁ ጊዜያት በባነር መልክ ታትመው የሚወጡ ሥዕሎችም በዓላቱ ሲያልፉና ተከብረው ሲጠናቀቁ ከተሰቀሉበት ሳይወርዱ ንፋስ ሲያዋዛውዛቸው የምንመለከትባቸውም አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ከተነሡም በኋላ ለበዓላቱ ተብለው ስለተዘጋጁ በክብር ቦታ ለጊዜው መቀመጥ ሲገባቸው እንደማንኛውም ባነር ተጠቅለው ጥግ ላይ ወድቀው ሊታዩ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በአንድም በሌላም መንገድ ቅዱሳት ሥዕላትን ማክበር እንዳለብን ብናምንም በተለያዩ ምክንያቶች በዝንጋኤ፣ ባለማወቅ፣ በድፍረት በማይገባ መንገድ የመያዝ ልመድ ያለባቸው ምእመናን አልፎ አልፎ ይታያሉ፡፡ ከዚህ ስንፍና መራቅ የሚገባ ነው፡፡

ቅዱሳት ሥዕላትን በተቻለ መጠን በዓላማ ማምጣት ይገባል፡፡ ለማምጣት መነሣት ብቻ ሳይሆን እንዴት ተከብረው እንደሚያዙም ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ የት በክብር አስቀምጣቸዋለሁ፣ እንዴትስ አስቀምጣቸዋለሁ፣ ለምን ለምን አገልግሎት እጠቀምባቸዋለሁ፣ ማን ይጠብቃቸዋል እያልንም ማሰብ አለብን፡፡

በምናደርገውና በምንይዘው ነገር ውስጥ ቅዱሳት ሥዕላትን የሚያቃልል ነገር ምን አለ ብሎ ማሰብ ይገባል፡፡ ቅዱሳት ሥዕላትን አክብሮ ለመያዝ ምን ምን ማድረግ እንደሚገባ ጠይቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ቅዱሳት ሥዕላቱን የቱን ነው የምገዛው? የምገዛው በምን ላይ የተሣሉትን ነው? አክብሮ ለመያዝ የሚረዳኝ መጠንና የተሠራበት ቁስ የትኛው ቢሆን ይሻለኛል? ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

ቅዱሳት ሥዕላቱን ይጠቀሙናል ብለን እስካመንን ድረስ ለበጎ የሚሆኑልን፣ የምንሻውን መንፈሳዊ ጸጋ የሚያስገኙልን አክብረን ስንያዛቸው ብቻ መሆኑን ማማን ይገባል፡፡ ‹‹ክብር ለሚገባው ክብር ስጡ›› እንደተባለ በረድኤት የማይለየንን እግዚአብሔርን ሥራና በአጸደ ነፍስ የሚያማልዱንን ቅዱሳን የምንዘክርባቸው ሥዕሎች ክብር ሊያገኙ ይገባል፡፡

# ፈትቼ ሳላገባ ብኖርስ!

***ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። በምሥጢሬን ዓምድ ላይ የምታወጧቸውን አስተማሪ እና የሰውን የውስጥ ችግር የሚፈቱ ጽሑፎች እከታተላለሁ፤ በዚያም ብዙ ትምህርቶችንና ቁም ነገሮችን አግኝቼበታለሁ ለዚያም የዓምዱን አዘጋጆች ከልብ አመሰግናለሁ። እኔም ውስጤ የሚመላለስ ጥያቄ ኖረና ወደ እናንተ ልጽፍ ወደድኩ። ስሜ ኃይለ ገብርኤል ይባላል የምኖረው እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ከባለቤቴ ጋር ልንስማማ አልቻልንም፤ በነገሮች ሁሉ አንጻ ግራንጻ የበዛው ኑሮ ለመግፋት ተገድጄአለሁ። ከዛሬ ነገ ይሻላል ብዬ ባስብም ከጊዜ ጊዜ ኑሮአችን ከመቃወስ አልዳነም። የተጋባነው በተክሊል ሥርዓት መሆኑ ለእስከ አሁኑ ታግሼ እንድኖር ምክንያት ሆኖኛል። ሌላው እስከ አሁን ለመታገስ ምክንያት የሆነኝ የሁለት ልጆቼ ጉዳይ ነው። ልጆቼን በቅርብ ሆኜ ማሳደግ ወደማልችልበት ሁኔታ ውስጥ መግባት አለመፈለጌ ነው። አሁን ግን በውስጤ የሚመላለሰውን ሐሳብ ፈትቼ ሌላ ማግባት ኃጢአት ከሆነብኝ፣ ፈትቼ ሳላገባ ብኖር ምን ክፉት አለው የሚል ነው። በልጆቼም በኩል ሰላም በሌለበት ቤት ውስጥ ማደጋቸው ተለይቼ ብወጣ ከሚደርስባቸው ጉዳት አይበልጥም የሚል ነው። በዚህ ላይ የእናንተ ምክር ምንድነው?***

ውድ ጠቂያችን! ምክራችንን ፈልገው ለላኩልን ጥያቄ ከፍተኛ አክብሮት አለን። ከጋብቻ ሕይወት ጋር ተያይዞ ያነሡልን ጥያቄ እርስዎ ያንሡት እንጂ ለሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ጥያቄ ላላቸው ወገኖችም ምክር ለመስጠት የሚያስችል ጥያቄ ነው።

በክርስትና ሃይማኖት ሰዎች የሚመርጡት ሕይወት ሁለት ነው፤ አንዱ በድንግልና ጸንቶ በምንኵስና ሕይወት ከዓለም ተለይቶ እግዚአብሔርን ለማስደሰት በእግዚአብሔር ረድኤት ታግዘን ተወስነን መርጠን ፈቅደን የምንይዘው ሕይወት ነው። ይህ ሕይወት ለክርስቶስ ፍቅር ሕይወታችንን በመስጠት ያለንን እምነትና ታማኝነት የምንገልጽበት ሕይወት ነው። ምንኵስና የዚህን ዓለም ጣዕም ንቆ የላመ የጣመ ሳይሹ፣ መድመቅ መብረቅረቅ ሳይፈልጉ፣ ለመሾም ለመሸለም ሳይጓጉ እግዚአብሔርን ብቻ ለማገልገል ወስኖ የሚገባበት ሕይወት ነው። ይህን ሕይወት የመረጠ ሰው ቤተ ክርስቲያን ባሏት ገዳማት ተወስኖ፣ በገዳማዊ ሥርዓቱ መሠረት የሚኖር ነው።

ሰው ስለ ክርስቶስ ደሙን እስከማፍሰስ በፍጹም ፍቅር በዓለሙ ሁሉ እየዞረ በማስተማር ከሚመርጠው የሰማዕትነት ሕይወት፣ ወይም ደግሞ በገዳማት ተወስኖ በጾም በጸሎት በመንፈሳዊ ተጋድሎ ከመኖር ባሻገር ‹‹በዓለሙ ውስጥ ሆኜ፣ ክርስቲያን ተብዬ፣ የክርስቶስን ሕጉን ትእዛዛቱን ጠብቄ እኖራለሁ›› ብሎ ሲመርጥ ደግሞ በጋብቻ መወሰነን ይመርጣል። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ በግልጽ ሲናገር ‹‹ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም። ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ። ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ፦ እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው፤ ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።›› ብሏል። (፩ኛ ቆሮ ፯-፱)

ከዚህ ውጪ ያለው የአኗኗር ምርጫ ግን ለፈተናና ለኃጢአት ሥራ የሚያጋልጥ ነው። አንዱ ለፈተና አጋላጭ የሚባለው ሕይወት ሳያገቡም ሳይመነኩሱም ተዘልሎ መቀመጥ ነው። ይህም በብዙ ምክንያቶች ሕይወታችንን ግራ የተገባ ሊያደርገው ይችላል። በርካቶች በዚህ ምርጫ ውስጥ ሲመላለሱ ይታያል። ነገር ግን ሕይወታቸው በወጥመድ የተከበበ ነው። ‹‹ከዛሬ ነገ አገባለሁ›› በሚል ማመንታት የሕይወት ምርጫቸውን ሳይወስኑ ዘግይተው፣ በመጨረሻ ለምርጫዎቻቸው ምቹ ባልሆነ ሥነልቦናና አካላዊ ሁኔታ ላይ ይደርሳሉ። ‹‹እናግባ›› ሲሉ በፈቃዳቸው የሚሹትን የመረጡትን የወደዱትን የፈቀዱትን ለማግባት ከዕድሜ የመነጨ፣ ከአካላዊ ለውጥ የመነጨ ሳንካ ያጋጥማቸዋል። ‹‹እንመንኩስ››ም ሲሉ የሚሰግዱበት ጉልበት፣ ከገዳም ገዳም ተመላልሰው የሚሹትን ያህል መንፈሳዊ ተጋድሎ ፈጽመው ለመገኘት የሚያስችል ሁኔታ ላይ አለመሆናቸውን ሲያስቡ ማመንታት ውስጥ ይገባሉ።

በዚህ ሂደት ውስጥ በድንገት፣ ያለፍላጎት፣ በመደናበር የሚገቡበት ሕይወት ሲኖራቸው ደግሞ አክብሮ ለመያዝና ለመቀበልም ይቸገራሉ። በመረጡት ምርጫ አለመርካት ወይም መቆጨትን ሊያስከትልባቸው ይችላል። መጽሐፍ ሁሉም በጊዜው ውብ እንደሚሆን እንዳመለከተን ሁሉ ዕድሜም በየምዕራፉ ለሕይወታችን የሚጋብዘው ምርጫ አለው። ይህን ዕድሜ የሚያቀርብልልን ምርጫ በጸሎትና በጾም ታግዞ አንዱን መቀበል የእኛ ፈንታ ይሆናል።

ውድ ጠያቂያችን እርስዎም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሚገባው ጊዜ በሥርዓተ ተክሊል የመሠረቱት ጋብቻ አለ። ክርስቲያን እንደመሆንዎ ክርስቲያናዊ ከሆኑ የሕይወት ምርጫ ዎች አንዱ የሆነውን በጋብቻ መወሰንን መርጠው መኖርና የልጅ ፍሬም አይተዋል። በዚህ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ ይገባል።

መረዳት የሚገባዎት ወሳኝ ነገር ግን በእያንዳንዱ ክርስቲያናዊ የሕይወት ምርጫዎቻችን ውስጥ ራሱን የቻለ ፈታኝ ገጽታም አለው። አንድ ሰማዕትነትን የመረጠ ክርስቲያን የአረማውያንን ሰይፍ ለመታገስ ቆርጦ መግባቱን እንረዳለን። አንድ መነኮስ ደግሞ ጸብአ አጋንንቱን ግርማ ሌሊቱን መታገስ፣ በብዙ ጾምና

ጸሎት ምስጋናም ምክንያት የሚመጣ የሥጋ ድካምን መታገስ ይጠበቅበታል። እነዚህ ሁሉ የትዕግሥት መከራ የመቀበል፣ ጸጋን ደግሞ የመልበስ ምልክት በሆነው ክቡር መስቀል ተባርከው የሚሰጡ ሕይወቶች ናቸው።

እንዲሁ ጋብቻም የምንታገሰው ብዙ ገጽታ አለው። በዓለም ውስጥ በጋብቻ መወሰን ማለት ቀላል ሕይወት መምረጥ ማለታችን አይደለም። የምንታገሰውን የመከራ ዓይነት መምረጥ ማለታችን እንጂ። የጋብቻን ሕይወት የሚመርጥ ሰው በመስቀል ኃይል ተባርኮ በሚገባበት ምሥጢረ ተክሊል ውስጥ ትዕግሥትንም ለመላበስ ቃል የምንገባበት ነው። በጋብቻ ውስጥ የምንታገሰው ብዙ ነገር አለ።

ጋብቻ ለራስ ብቻ ሳይሆን ለትዳር አጋር ኃላፊነት የምንወስድበት፣ ከዚያም አልፎ ተባርከው ለሚሰጡን ልጆች ኃላፊነት የምንወስድብት ሕይወት ነው። እነዚህ አብረውን የሚኖሩ እያንዳንዳቸው የቤተሰብ አባላት የየራሳቸው ፈቃድ ያላቸው በመሆኑ በኑሮና አኗኗር ውስጥ በሚኖራቸው ልዩ ልዩ ፍላጎትና ስሜት ምክንያት የቤተሰቡ ኃላፊነት ያለባቸው ባል ወይም ሚስት አጋራቸውን ብቻም ሳይሆን አጠቃላይ የቤተሰቡን አባላት የመታገስ ኃላፊነት አለባቸው።

ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ተጠብቃ የምትኖረው በትዕግሥታችን ነው። ወንጌል ‹‹በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ።›› (ሉቃ ፳፩፥፲፱) በኑሮ ውጣ ውረድ ምክንያት አስቀድመው ወደው መርጠው ያገቧትን ሚስትዎን መፍታት የሚገባ አይደለም። ለክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ያለው ኑሮ ከመከራ የተለየ አይደለም። ስለዚህ ከቤተሰባችንም የሚመነጭ መከራ ሊመጣ ይችላል። በትዳር አጋሮቻችን ላይ ድክመቶች ሊታዩ ይችላሉ። እንደ ኢዮብ ሚስት ሰነፍ ሚስት፣ እንደ አቤጊያ ባል ሰነፍ ባሎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ልንታገሳቸው ግን ግድ ነው። ሰዎች ሚስት ወይም ባል ሲያገቡ ሁሉን ነገራቸውን ወደውላቸው ላይሆን ይችላል፤ ልንታገሳቸው ፈቅደን የምንቀበልላቸው ድክመት ሊታይባቸው ይችላል። ይህ ድክመት በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀረፍ ወይም ሊቀጥል ይችላል። ነገር ግን ለመፍታት የሚያበቃ ምክንያት እስከልሆነ ድረስ ከመታገስ ውጪ አማራጭ አይኖርም።

አንድ ወንድ ወይም ሴት ሚስቱን ወይም ባሏን የምትፈታው በማመንዘር የተገለጸ ኃጢአት ስትሠራና ሲሠራ ነው። ጌታችንም ሲያዘን ‹‹ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።›› ብሏል። (ማቴ ፭፥ ፴፪) አስቀድሞ በተጠቀሰው በዝሙት ምክንያት ወይም በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በተክሊል የተመሠረተ ትዳርን ማፍረስ ተገቢ አይደለም።

ውድ ጠያቂያችን! እርስዎ እንዳሉት ከፊቱ አለማግባትን ምክንያት አድርጎ ሚስትን መፍታት እጅግ ከባድ ፈተናን በራስና በትዳር አጋር ላይ ማምጣት ነው። ‹‹ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥›› የሚለው ከላይ የተጠቀሰውን ቃል አጥር ማድረግ ያስፈልጋል። ለመጋባት የገባችሁትን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ትዕግሥት ካጣችሁ፣ ከተፋቱ በኋላ ሳያገቡ ለመኖር የሚገኝ ትዕግሥት ከወዴት ይመጣል? ይህ ቢሆን እንኳን በሁለቱም ተጋቢዎች ፈቃድ ነው፤ አንዱ ቢበረታ ሌላው ሊረታ ይችላልና ይህም ከባድ ፈተና ያስከትላል። ሌላ ላለማግባት ወስነው የሚለያዩ ባለትዳሮች በሆነ አጋጣሚ ማግባት ቢፈልጉ እንኳን ከትዳር አጋራቸው ውጪ ሌላ የማግባት ሥልጣን የላቸውም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ስላሉት ሲናገር ‹‹ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፥ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ፥ ባልም ሚስቱን አይተዋት ብዬ የተጋቡትን አዛቸዋለሁ፥ እኔ ግን አላዝም፥ ጌታ እንጂ።›› (፩ኛ ቆሮ ፲-፲፩) ብሏል።

ውድ ጠያቂያችን! ማስተዋል ያለብዎት ነገር እርስዎ ስለሚያገኙት ዕረፍት ብቻ ሳይሆን የትዳር አጋርዎ ስለሚያጋጥማቸው የሕይወት ቀውስም ነው። እርስዎም ዕረፍት ስለማግኘትዎ ዋስትና አይኖርዎትም። ክርስቲያን ይፈተናል፤ የፈተና ዓይነቱ እንደ ደረሱበት የሕይወት ምዕራፍ ልዩ ልዩ ነው። ከሥጋችን የመነጨ ብቻ ሳይሆን ከአጋንንት ትንኮሳ የመነጨ ፈተና ብዙ አለ።

ከዚያ አልፎ ደግሞ ኑሮ ሲናጋ በልጆችና በአጠቃላይ ኑሮ ውስጥ የሚመጣ ቀውስም ዕድሜን፣ ስሜትን፣ ሀብትን፣ ማኅበራዊ ግንኙነትን የሚያባክንብን ነው። እነዚህን የሚያባክኗቸውን ነገሮች በትዕግሥት መታደግ ሚስት ከዝሙት በመለስ የምታመጣውን ፈተና ለመታገስ ይበጃል።

ከትዳር አጋር የሚመጣ ፈተናን ለመቋቋም ደግሞ የሚሻለው በቅርበት ባሉ የነፍስ አባት የሚቻለውን ያህል በግልጽ መመካከር አግባብ ነው። ከነፍስ አባት ባሻገርም ቤተሰቡ የሚያከብራቸው፣ የሚያምናቸውን ቅርብ ሰዎችን ይዞ መመካከር ዕረፍትን ያስገኛል። በጋብቻ ሕይወታችን ፈተናዎች ጠንክር ብለው የሚመጡት በመንፈሳዊ ሕይወት ዝለት ሲያጋጥም ነው። በመሆኑም ሕይወትን ወደ ቤተክርስቲያን መመለስ፣ ከመንፈሳዊ ሕይወት አለመለየት፣ ከቃለ እግዚአብሔር አለመለየት ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ሕይወታችን ያጋጠመንን የኑሮ ደዌ ባይፈውስ እንኳን የምንችልበትን ኃይል ያጎናጽፋል።

ውድ ጠያቂያችን! ስለእግዚአብሔር ብሎ በትዕግሥት ጋብቻን ማጽናት ያስፈልጋል። በተጨማሪ ደግሞ ስለሚወዷቸው፣ ስለሚሳሱላቸው ልጆች ብለው በኑሮ ውስጥ የሚመጣን ፈተና በትዕግሥት መቀበል ለድል ያበቃል። ለጥቂት ጊዜያት የምንቀበለው መከራ የብዙ ዘመን ፍስሓ የሚሆን ጸጋን ሊያጎናጽፈን እንደሚችል ማመን ይገባል።